## ምዕራፍ፡ ፴፪፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ፡ ናፖሊዮን፡ ቦናፓርት፡ አወዳደቅ ።

፩፤ በሺ፡፯፻፺፱፡ ቦናፓርት፡ የፈረንሳይ፡ ሬፑብሊክ፡ አማካሪ፡ ተብሎ፡ ለዕድሜ፡ ልኩ፡ ተመረጠ ። ሁለት፡ ዓመት፡ ከቈየ፡ በኋላ፡ ናፖሊዮን፡ ተብሎ፡ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ሆነ ። ከቀድሞ፡ ነገሥታት፡ ይልቅ፡ ኀይልና፡ ሥልጣኑ፡ ያለመጠን፡ የበረታ፡ እርሱ፡ ነበር ።

፪፤ ይህ፡ ታላቅ፡ ካፒቴን፡ በመላ፡ ኤውሮጳና፡ በተጓዘበት፡ስፍራ፡ ሁሉ፡ ለመከተል፡ አልቻልሁም ። ተዋግቶም፡ ያገኘውን፡ ድል፡ ለመቍጠር፡ አልችልም ። በሄደበት፡ ስፍራ፡ ሁሉ፡ ነገሥታት፡ እየመጡ፡ እጅ፡ ይነሡት፡ ነበር ። እርሱም፡ ከዙፋናቸው፡ እያወረደ፡ በስፍራቸው፡ ወንድሞቹንና፡ ታላላቆቹን፡ የራሱን፡መኳንንት፡አስቀመጠበት፡የነገሥታትን፡ዘውድ፡እንደ፡መጫወቻ፡ አድርጎ፡መለሰላቸው። ዕድሉ፡ ሁልጊዜ፡ ድል፡ እንዲያገኝ፡ ስለ፡ አደረገለት፡ ዕድላም፡ ይሉት፡ ነበር ።

፫፤ ዳሩ፡ ግን፡በሺ፡፰፻፲፪፡የመከናወኑ፡ መንገድ፡ ይሰናከልበት፡ ጀመር ። ታላቅ፡ ጦር፡ አስከትቶ፡ መስኮብን፡ ወረረና፡ እከተማው፡ እመስኮብ፡ ድረስ፡ ቀድዶት፡ ስለ፡ገባ፡ መስኮቦች፡ የገዛ፡ ከተማቸውን፡ እሳት፡ለቀቁበት ። ክረምቱ፡ ተቃርቦ፡ ነበርና፡ የፈረንሳይ፡ ወታደሮች፡ የሚጠጉበት፡ ስፍራ፡ አላገኙም ።

፬፤ ወደ፡ ፖላንድ፡ ተመልሰው፡ ሲሄዱ፡ ሳሉ፡ በመንገድ፡ ከመስኮቦች፡ ጋር፡ ሲዋጉ፡ አየሩ፡ ያለመጠን፡ብርድ፡ ስለ፡ሆነ፡ የሞቱት፡ ሬሳ፡ እንደ፡በረዶ፡ጠጥሮ፡ በረዶው፡ ከደማቸው፡ ጋር፡ ተዋሐደና፡ ደም፡ መሰለ ።

፭፤ ወደ፡ ፖላንድ፡ ወሰን፡ ሳይደርሱ፡ ከጦራቸው፡ አንድ፡ እጅ፡ ሲቀር፡ ሦስቱ፡ እጅ፡ ስለ፡ተበላሸባቸው፡ ንጉሠ፡ናፖሊዮን፡ ባንዲት፡ ሠረገላ፡ ተቀምጦ፡ሸሸና፡ ወደ፡አገሩ፡ ወደ፡ፓሪስ፡ ተመልሶ፡ ወዲያው፡ቶሎ፡ ብሎ፡ አዲስ፡ጦር፡ሰበሰበና፡ ሊዋጋ፡ ተሰናዳ ።

፮፤ ነገር፡ ግን፡ የኤውሮጳ፡ ሕዝብ፡ ባንድነት፡ ተስማምተው፡ በርሱ፡ ላይ፡ ተነሡብትና፡ ጥቂት፡ ከተዋጉ፡ በኋላ፡ ከጀርመኖች፡ፊት፡ ወደ፡ ኋላው፡ እያፈገፈገ፡ ወደ፡ ፈረንሳይ፡ ደረሰ ። ጠላቶቹም፡ ተከታትለው፡ በሜዴቴራኒያን፡ ውስጥ፡ ባለችው፡ ኤልባ፡ በምትባል፡ በትንሽ፡ ደሴት፡ ውስጥ፡ የፈረንሳይን፡ የንጉሥ፡ ዘውድ፡ እንዲያስረክብ፡ አስገደዱት ።

፯፤ ናፖሊዮን፡ ወደ፡ ኤልባ፡ ሄደና፡ አንድ፡ ዓመት፡ ያህል፡ ተቀመጠ ። ስለ፡ሆነ፡ በመጋቢት፡ ወር፡ በሺ፡፰፻፲፭፡ ዓመት፡ በድንገት፡ ተነሥና፡ ወደ፡ ፈረንሳይ፡ ጠረፍ፡ ብቅ፡ አለ ። ወደ፡ጠረፍ፡ በደረሰ፡ ጊዜ፡ ፈጽሞ፡ ብቻውን፡ ነበር፤ በዚያ፡ አውራጃ፡ ለማየት፡እንኳ፡ የሚያስፈሩ፡ የርሱ፡የቀድሞ፡ ወታደሮቹ፡ ነበሩ፤ እነዚህ፡ ባዩት፡ ጊዜ፡ በደስታ፡ እልል፡ አሉ ። ከርሱ፡ በኋላ፡ የነገሠውን፡ የቡርቦንን፡ ንጉሥ፡ (የንጉሥ፡ ተወላጅ )፡ነጭ፡ ባንዲራ፡ በእግራቸው፡ ረጋገጡትና፡ ከጥቂት፡ ቀን፡ በኋላ፡ የናፖሊዮን፡ ባንዲራ፡ በፈረንሳይ፡ አውራጃ፡ ሁሉ፡ ድል፡ እያደረገች፡ ትውለበለብ፡ ጀመረች ።

፯ ፤ የኤውሮጳም ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ጦራቸውን ፡ ሰብስበው ፡ የዌሊንግተን ፡ ዱክ ፡ በሚባል ፡ ሰው ፡ ይመሩ ፡ ነበር ፤ ናፖሊዎንም ፡ ወደ ፡ ፍላንደርስ ፤ ወይም ቤልጊዩም ፡ ሊገናኛቸው ፡ ሲጓዝ ፡ ጠመንጃ ፡ የተሸከመ ፡ የፈረንሳይ ፡ ወጣት ፡ ሁሉ ፡ ተከትሎት ፡ ነበር ።

፰ ፤ ንጉሥ ፡ ናፖሊዎን ፡ በኋለኛው ፡ በመጨረሻው ፡ ጦርነት ፡ ሰኔ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ሺ ፡ ፰፻፲፭ ፡ ዋቴርሎ ፡ ላይ ፡ ተዋጋና ፡ በዚያ ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ ተሸረ ፡ ፈረንሳይም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ተሻረች ። ጦረኛው ፡ ንጉሥ ፡ በዚያ ፡ እንዲሞት ፡ ሔሊና ፡ ወደ ምትባል ፡ ደሴት ፡ ከሰደዱት ፡ በኋላ ፡ የቡርቦን ፡ ንጉሥ ፡ መንግሥቱ ፡ ጸናለ ትና ፡ በሉዊስ ፡ አሥራ ፡ ስድስተኛ ፡ ዙፋን ፡ ተቀመጠ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ የናፖሊዎን ፡ ማዕርግ ፡ ምንድነው ፡ ?
፪ ፤ በየሄደበት ፡ ሁሉ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ምን ፡ ይባል ፡ ነበር ፡ ?
፫ ፤ በ፲፰፻፲፪ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ? የፈረንሳይ ፡ ጦር ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፬ ፤ ናፖሊዎን ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፭ ፤ ምን ፡ ተደረገለት ፡ ?
፮ ፡ ናፖሊዎን ፡ በኤልባ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ቈየ ፡ ? በ፲፰፻፲፭ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ? ወደ ፡ ፈረንሳይ ፡ አገር ፡ አገባቡን ፡ ተናገር ።
፯ ፤ ለኤውሮጳ ፡ ነገድ ፡ መሪ ፡ ማን ፡ ሆነ ፡ ? ናፖሊዎን ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ? ማን ፡ ተከተለው ፡ ?
፰ ፤ የዋትርሎ ፡ ውጊያ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነበር ፡ ? የናፖሊዎን ፡ ፍጻሜ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፻፵፫ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፡ ፈረንሳይ ፡ አኳኋን ።

፩ ፤ ሉዊስ ፡ ዐሥራ ፡ ስድስተኛው ፡ አዲሱ ፡ የፈረንሳይ ፡ ንጉሥ ፡ የተከበረ ፡ ወፍራም ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ይልቁንም ፡ በጣም ፡ አድርጎ ፡ አይስትር ፡ የሚወድ ፡ ይመስላል ። በሺ ፡ ፰፻፳፬ ፡ ሞተና ፡ ወንድሙ ፡ ሻርል ፡ ዐሥረኛ ፡ የተባለ ዙፋኑን ፡ ወረሰ ።

፪ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ቡርቦንስ ፡ ባለፈው ፡ ፈተና ፡ ጥቅም ፡ አላገኙምና ፡ በሺ ፡ ፰፻፴ ፡ ሻርል ፡ ዐሥረኛ ፡ መንግሥቱና ፡ እርሱ ፡ የሚመሰገንበት ፡ ጕዳይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ጋዜጣ ፡ በማተሚያ ፡ ገብቶ ፡ እንዳይታተም ፡ ከለከለ ።

፫ ፤ የፓሪስ ፡ ሕዝብ ፡ ያንጊዜውን (ዐመፁና) አድማ ፡ አደረጉና ፡ የደረጃ ፡ ድንጋይ ፡ እያነሡ ፡ የንጉሡን ፡ ወታደሮች ፡ ራስ ፡ ይፈነክቱ ፡ ጀመር ፤ እንዲሁ ፡ አሮጌው ፡ ንጉሥ ፡ ራሱን ፡ የሚያስጠጋበት ፡ አጥቶ ፡ እስኪንገዳገድ ፡ ድረስ ፡ እየተኰሱ ፡ በጥይት ፡ ከየቤቱ ፡ መስኮት ፡ ወታደሮቹን ፡ ያንጠባጥቡዋቸው ፡ ጀመር ።

፬ ፡ እስኪ ፡ በትከሻዬ ፡ ልሸከመው ፡ አለና ፡ የወርቅ ፡ ዘውዱን ፡ ከራሱ ፡ ላይ ፡ አውልቆ ፡ በልጁ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ አኖረው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የፈረንሳይ ፡ ሕዝብ ፡ ይህ ፡ ሕፃን ፡ ንጉሣቸው ፡ እንዲሆን ፡ ስለ ፡ አልፈቀዱ ፡ ሻርልንና ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ እየገፈተሩ ፡ ካገር፡አስወጡዋቸው ።

፭ ፡ ሁለተኛው ፡ እርምጃቸው ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ አገዛዝ ፡ ለማቆም ፡ ነበርና ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ላፋየት ፡ ከተባለው ፡ ከተከበረው ፡ ጀኔራላቸው ፡ ጋር ፡ ለመ መካከር ፡ አሰቡ ። እንደርሱ ፡ አሳብ ፡ ቢሆን ፡ ሬፑብሊክ ፡ አገዛዝ ፡ እንዲሆን ፡ በወደደ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ አገዛዝ ፡ ለፈረንሳይ ፡ ሕዝብ፡ የማይስማማቸው ፡ መሆኑን ፡ ስለ፡ዐወቀ ፡ ሉዊስ፡ፊሊጵን ፡ ለንጉሥነት ፡ መር ጠው ፤ በንጉሥ ፡ እንዲገዙ ፡ መከራቸው ።

፮ ፡ በሺ፡፰፻፴ ፡ ሉዊስ ፡ ፊሊጵ ፡ ባልጋው ፡ ተቀመጠና ፡ ፈረንሳይን ፡ በጥንቃቄ፡ እየገዛ ፡ መንግሥቱን ፡ ከፍ ፡ ወዳለ ፡ ደረጃ አደረሰው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ፡ ወረተኞች ፡ የሆኑ ፡ ዜጎቹ ፡ በሺ ፡ ፰፻፵፰ ፡ መንግሥቱን ፡ እንዲለቅ ፡ አስገ ደዱት ።

፯ ፡ ከዚህማ ፡ ወዲያ ፡ የሚያስፈራ ፡ መለያየት ፡ ተነሣ ። እኩሌቶቹ ፡ የአገር፡ፍቅር፡ አለን ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ለጊዜው ፡ ብቻ ፡ የሚሆን ፡ አገዛዝ ፡ የሚሉትን፡አሳብ፡ አበጁ ። ነገር፡ግን ፡ ሽብር ፡ የሚያስነሡትን ፡ ሰዎች ፡ ጸጥ፡እንዲሉ ፡ አደርጋ ለሁ ፡ ብሎ ፡ የፈተነው ፡ የፓሪስ ፡ መልካሙ ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት ፡ ተገድሎአልና ፡ ይህም ፡ አልተወደደም ።

፰ ፡ በመጨረሻው፡የታላቁ፡ንጉሥ፡የናፖሊዮን ፡ የእኅት ልጅ፡ፕሪንስ ፡ ሉዊስ፡ ናፖሊዮን ፡ የተባለ ፡ በታኅሣሥ ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ሺ፡፰፻፵፰ ፡ ከፈረንሳይ ፡ ሬፑብ ሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ በታች ፡ ሆኖ ፡ ታላቅ ፡ ሹመት ፡ አገኘ ።

፱ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳ ፡ ፳፩ ፡ ሺ ፡ ፰፻፶፩ ፡ በባለሥልጣኖቹ ፡ አድርጎ ፡ ሕዝቡ ፡ የተ ሰበሰበበትን ፡ ጉዳይ ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ አደረሰው ። እንደ፡ገና ፡ ላሥር፡ዓመት፡ የሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ እንዲሆን ፡ ከሰባት ፡ ሚሊዮን ፡ በላይ ፡ በሚሆን ሕዝብ ፡ ተመረጠ ። ደግሞ ፡ በኅዳር ፡ ሺ፡፰፻፶፪ ፡ ከላይ ፡ ከዘር ፡ ተያይዞ ፡ የመ ጣለት ፡ ዘውድ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቍጥራቸው ፡ እነዚህኑ ፡ የሚያህሉ ፡ ሰዎች፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እንዲሆን ፡ መረጡትና ፡ ናፖሊዮን ፡ ፫ኛ ፡ ተብሎ ፡ በዙ ፋን ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ። በሺ፡፰፻፶፫ ፡ ከታላላቆች ፡ ወገን ፡ የተወለደች ፡ አንድ፡ የእስጳንያ ፡ ሴት ፡ አገባና ፡ በብርታትና ፡ በመከናወን ፡ ፈረንሳይን ፡ ዐሥራ፡ ስምንት ፡ ዓመት፡ ገዛ ።

፲ ፡ በዘመኑ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ እንዲቋቋም ፡ ረዳ ። የፈረንሳይ ፡ ገቢ ገንዘብና ፡ ንግድ ፡ በጣም ፡ እየተሻሻለ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ ፓሪስ ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ ገናና ፡ ሁኖ ፡ ነበር ። በሐምሌ ፡ ሺ፡፰፻፸ ፡ ፕሩስያን ፡ ለመውጋት ፡ ጦር ፡ ቢያ ውጅ ፡ ጀርመን ፡ ስምምነት ፡ አለውና ፡ ሊመልሰው ፡ ተነሣ ።

ጀርመኖች ፡ ወደ፡ፈረንሳይ ፡ ገቡና፡የናፖሊዮንን ፡ ጦር ፡ ፈጽመው ፡ ድል ፡ አደረጉት ። ናፖሊዮንንም ፡ ሲዳን ፡ በምትባል ፡ ስፍራ ፡ ማርከው ፡ ወደ ፡ ፕሩሲያ፡ ወሰዱት ፤ ንግሥቲቱ ፡ አንድ ፡ ልጅዋን ፡ ይዛ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ አመለጠች ። ጀርመኖችም ፡ በጦርነቱ ፡ እየገፉ ፡ ሄዱ ። ናፖሊዮን ፡ በሲዳን ፡ ከተማረከ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ ቶሎ፡ስለ፡ተለቀቀ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ፡አገር፡ተሻገረና፡ከሚስቱና፡ከልጁ ፡ ጋር ፡ ቺሰል ፡ ኸርስት ፡ ላይ ፡ በኬንት ፡ ከተገናኘ ፡ በኋላ ፡ ጥር፡፱፡ቀን፡ሺ፡፰፻፸፫ ፡ ከዚያው ፡ ሞተ ። ጥር፡፳፰፡ቀን፡ሺ፡፰፻፸፩ ፡ ፓሪስ ፡ ከተማው፡ተያዘና ፡ ጦርነቱ ፡ እንዲቆም ፡ ስምምነት፡ስለ፡ተደረገ ፤ የመንግሥታት ፡ መሰብሰብ ፡ ተጀመረ ። በዚህም ፡ መሰብሰብ ፡ ሚኒስትር ፡ ቲዬርስ ፡ የፈረንሳይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ እንዲሆን ፡ ተደረገ ። በየካቲት፡፳፮፡ቀን፡ሺ፡፰፻፸፩ ፡ በቤርሴል ፡ የዕርቅ ፡ ስምምነት ፡ ተፈረመ።በግንቦት፡፳፬፡ቀን፡ሺ፡፰፻፸፫፡የሕዝብ፡ጉባኤ፡ሻረውና ፡ሹመቱን ፡ ለቀቀ ። በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ማክማሆን ፡ ለሰባት ፡ ዓመት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ተብሎ ፡ እንዲሾም ፡ ተመረጠ ። በሺ፡፰፻፸፱ ፡ ሚስተር ፡ ጁለስ፡ግሬቪ ፡ በማርሻል ፡ ማክማሆን፡ስፍራ ፡ ተሾመ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ፲፰ኛ ፡ ሉዊስ ፡ የተባለው ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፪ ፤ ስለቡርቦን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ምን ፡ ተባለ ፡ ?

፫ ፤ በ፲፰፻፴-ምን ፡ ተደረ ፡ ?

፬ ፤ በፓሪስ ፡ የሚደረገው ፡ የሕዝብ ፡ ዱለት ፡ ምንድነው ፡ ?

፭ ፤ ላፋየት ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ምክር ፡ አቀረበ ፡ ?

፮ ፤ ሉዊስ ፡ ፊሊፕ ፡ የተባለ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፯ ፤ የርሱን ፡ ሥርዓትና ፡ ደንብ ፡ ምን ፡ ተከተለው ፡ ?

፰ ፤ ዋናውን ፡ ሥልጣን ፡ ማን ፡ ያዘው ፡ ? ምን ፡ ጊዜ ፡ ?

፱ ፤ ስለ ፡ ናፖሊዮን ፡ ፫ኛ ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ ?

፲ ፤ ጦርነት፡ያወጀው፡ምን፡ጊዜ፡ነው፡?ጦርነትን፡የጫነው፡በማን፡ላይ፡ነው፡? በምን ፡ የተነሣ ፡ ? ቀጥሎ ፡ ምን ፡ ያልታሰበ ፡ ነገር ፡ ሆነ፡? ቀጥሎ ፡ ወዲያው ፡ ምን ፡ ሆነ፡?

የፈረንሳይ ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

የፈረንሳይ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ማነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፮፻፱ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፡ ጀርመን ።

፩ ፤ ስድ ፡ የነበረው ፡ የጥንት ፡ የጀርመን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛት ፡ ባ፲፰፻፮ ፡ ወደ ሠላሳ ፡ ዘጠኝ ፡ መንግሥታት ፡ ሁኖ ፡ ተከፋፈለና ፡ በሺ ፡ ፰፻፲፭ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በስም ምነት ፡ ተሠራ ። እነዚህም ፡ በንድነት ፡ የተገናኙ ፡ የጀርመኖች ፡ መንግሥታት ፡ ተባሉ ። እነዚህም ፡ መንግሥታት ፡ ነጻነት ፡ ባላቸው ፡ ገዦች ፡ ይገዛሉ ። ከነዚ ህም ፡ ታላላቆቹ ፡ የኦስትሪያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤ የፕሩሲያ ፡ ንጉሥ ፤ የባቫሪያ ፡ ንጉሥ ፤ የሳክሰን ፡ ንጉሥ ፡ የሀኖብር ፡ ንጉሥ ፤ የዋርትንቡርግ ፤ ንጉሥ ፡ ናቸው ። የቀሩት ፡ ሌሎቹ ፡ በዱኮችና ፡ በፕሪንሶች ፡ ሲገዙ ፡ ቈይተው ፡ ከነዚህ ፡ እምስቱ ፡ በመሻርም ፡ በመጥፋትም ፡ በሹመት ፡ ማቋረጥም ፡ ተውጠው ፡ ቀሩ ።

፪ ፤ እነዚህም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መንግሥታት ፡ ወደሚሰበሰቡበት ፡ ፍራንክፎርት ፡ ወደተባለው ፡ ነጻ ፡ ከተማ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ መልክተኞቻቸውን ፡ ይልካሉ ። ይህም ፡ የመላው ፡ መንግሥታት ፡ ዋና ፡ መሰብሰቢያ ፡ ነው ። ይህም ፡ ደንብ ፡ እስከ ፡ ሺ ፡ ፰፻፷፮ ፡ ጸንቶ ፡ ቈይቶአል ። በኦስትሪያና ፡ በፕሩሲያ ፡ መኻከል ፡ ጦርነት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከጥቂት ፡ ዘመቻ ፡ በኋላ ፡ ፕሩሲያ ፡ ድል ፡ አደረገ ። ኦስትሪያም ፡ ከጀርመኖች ፡ ጋር ፡ ከነበረው ፡ ስምምነት ፡ ተዘጋ ።

፫ ፤ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ የቆመበት ፤ ሚያዝያ ፡ ፲፮ኛ ፡ ሺ ፡ ፰፻፸፩ ፡ ዓ. ም. ነው ። በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ የጀርመን ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ መንግሥቱን ፡ ለመጠ በቅና ፡ ለጀርመን ፡ ሕዝብ ፡ እኑዋኑር ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲደረግ ፡ የዘለዓለም ፡ አንድ ነት ፡ እንዲቆም ፡ የወሰኑ ፡ ፳፭ ፡ መንግሥታት ፡ ናቸው ። ስማቸውም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ።

ፕሩሲያ ፡
ባቫሪያ ፡
ወርቴምበርግ ፡
ሳክሶኒ ፡
ቤድን ፡
ሜክለንቡርግ ፡ እስክዌሪን ፡
ሄስ ፡
ኦልድንቡርግ ፡
ሳክሴ ፡ ዌሚር ፡
ሜክለንቡርግ ፡ እስትሬሊትዝ ፡
ብሩንስዊክ ፡
ሴክስ ፡ ማይኒንግን ፡
እንሃልት ።

ሳክስ ፡ ኮቡርግ ፡ ጎታ ፡
ሳክስ ፡ አልቴንበርግ ፡
ዋልዴክ ፡
ሊፕ ፡
ሽዋርዝበርግ ፡ ሶንድርሻውስን ፡
ነውስ ፡ ሼላይዝ ፡
ሻውምቡርግ ፡ ሊፕ ፡
ሩስ ፡ ግራይዝ ፡
ሀምቡርግ ፡
ሉቤክ ፡
ብሬምን ፡
ራይሻስተንድ ፡ የአልሳስ ፡ ሎራይን ።

፬ ፤ ዋና ፡ ከተሞች ፡ የተባሉት ፡ እሊህ ፡ ናቸው ። የጀርመን ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ በርሊን ፡ ናት ፤ የፕሩሲያ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ሙኒሽ ፡ ናት ፤ እርስዋም ፡ የጀርመን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዋና ፡ ግዛት ፡ ነች ፤ የባቫሪያ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ድሬስድን ፡ ናት ፤ ይህችም ፡ እጅግ ፡ ያማረች ፡ ከተማ ፡ ናት ። የሳክስን ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ከርስሩህ ፡ ነች ። ይህችም ፡ ከኤውሮጳ ፡ ከተሞች ፡ ጥሩ ፡ ሆና ፡ የተሠራች ፡ ናት ። የቤድን ፡ ዋና ፡ ከተማና ፡ ሌሎችም ፡ እንደዚሁ ፡ ትክክል ፡ ሁነው ፡ የተሠሩ ፡ አሉ ። ዋኖች ፡ ወንዞችም ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። ዳኑብ ፤ ራይን ፤ ዋስር ፡ ኤልብ ፤ ኤደር ፤ ሜንም ፤ እነዚህና ፡ ሌሎችም ፡ አርባ ፡ የሚሆኑ ፡ መርከብ ፡ የሚሄድባቸው ፡ አሉ ።

፭ ፤ ጀርመን ፡ ታላቅ ፡ ሥልጣኔ ፡ አግኝቶአል ፤ ዛሬም ፡ ቢሆን ፡ በጦር ፡ ወታደር ፡ በኩል ፡ ከኤውሮጳ ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ነው ። ጀርመኖች ፡ በመልካም ፡ አስተዳደግ ፡ አድገዋል ። (ተምረዋል) ፡ በንግድና ፡ በብልሀት ፡ ሥራ ፡ እጅግ ፡ ገፍተዋል ። አንድነታቸው ፡ ኃይል ፡ ሰጥቶአቸዋል ። እያንድ ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ ወታደር ፡ እንዲ ሆን ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

ጥያቄ ።

፩ የጥንት ፡ ጀርመን ፡ የተከፋፈለው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? እንደምን ፡ ነበር ፡ ? እነዚህ ፡ አውራጃዎች ፡ እንደምን ፡ ይገዙ ፡ ኑረዋል ፡ ?

፪ ፤ በፕሩሲያና ፡ በአውስትሪያ ፡ መኻከል ፡ ጦርነት ፡ የተደረገው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? ምክንያቱ ፡ ምንድን ፡ ነበር ፡ ?

፫ ፤ በመንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ስንት ፡ ትንንሾች ፡ መንግሥታት ፡ ነበሩ ፡ ? ስማቸውን ፡ ተናገር ።

፬ ፤ በጀርመን ፡ ታላላቅ ፡ ከተሞች ፡ የተባሉት ፡ እነማናቸው ፡ ? ወንዞቹስ ፡ ? የጀርመን ፡ የጦር ፡ ኃይል ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ትምህርቱ ፤ የረቀቀው ፡ ብልሀቱ ፤ ንግዱስ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

ምዕራፍ ፡ ፪፵፭ ፡ ኤውሮጳ ።

ስለ ፡ ጥንታውያን ፡ ነገደ ፡ ጀርመንና ፡ ስለ ፡ ሻርለማኝ ስለ ፡ ሌላም ፡ ሁሉ ።

፩ ፤ እንደ ፡ ነገርኋችሁ ፡ ጥንት ፡ ዘመን ፡ ጀርመኖች ፡ ነገደ ፡ አራዊት ፡ ተብለው ፡ ቊጥራቸው ፡ የበዛ ፡ ባላገሮች ፡ ነበሩ ። ከነዚህም ፡ መኻከል ፡ ጎቶች ፤ ቪዚጎቶች ፤ ዋንዳሎች ፤ ሱዌቪ ፤ ሲምብሪ ፤ ቲውቶን ፤ ሄሩሊ ፤ አልማኒ ፡ የተባሉና ፡ ሌሎችም ፡ ብዙዎች ፡ ነበሩ ፤ ሁለትና ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ነበረው ፡ የምናውቀው ፡ እጅግ ፡ ጥቂት ፡ ነው ።

፪ ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጥቂት ፡ ነበሩ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ አራዊት ፡ ጨካኞች ፡ ነበሩ ። ልብሳቸው ፡ ያውሬ ፡ ቆዳ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ለጦርነትና ፡ ለዘረፋ ፡ ጊዜ ፡ ይመቻቸው ፡ ነበር ። በቄሣር ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ኀይለኞች ፡ ሆነው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ያ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ጀግና ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ጦርነት ፡ አንሥቶ ፡ ገሠገሠባቸውና ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ ከፈሰሰ ፡ በላይ ፡ አስገበራቸው ።

፤ ሮማውያን ፡ በሄዱባቸውና ፡ ወይም ፡ እጃቸውን ፡ በዘረጉባቸው ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡
ብልሀታቸውን ፡ ይዘው ፡ ይሄዳሉ ፡ ብዬ ፡ አስቀድሜ ፡ ነግሬያችኋለሁ ። ስለዚህ ፡
ባሌጌውና ፡ ደደቡ ፡ የጀርመን ፡ ሕዝብ ፡ ጥቂት ፡ ሥልጣኔ ፡ አገኘ ፤ ከሕዝቡም ፡
አያሎች ፡ ያሸነፍጡት ፡ የነበረውን ፡ የአውሬ ፡ ቆዳ ፡ እያስቀመጡ ፡ የሮማውያንን ፡
ነጠላ ፡ መለጠፍ ፡ (ማገልደም) ፡ ለመዱ ። ደግሞም ፡ ከጥንታቸው ፡ የተሻለ ፡ የጦር ፡
መሣሪያና ፡ የተሻሉ ፡ ቤቶች ፡ መሥራት ፡ በምቾት ፡ መኖርንም ፡ ሁሉ ፡ ተማሩት ።
፲፩ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከቄሣር ፡ በኋላ ፡ አራት ፡ ወይም ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ባለፈ ፡ ጊዜ ፡
ሮማውያን ፡ ለመውደቅ ፡ መርገድገዳቸውን ፡ አሳስባችኋለሁ ። ስለዚህ ፡ እነዚህን ፡
ዕረፍት ፡ የሌላቸውን ፡ ነገዶ ፡ ሰሜን ፡ ጸጥ ፡ አድርጎ ፡ ለመግዛት ፡ የማይቻል ፡ ሆነ ።
ሮም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ራሱን ፡ እንኳ ፡ ለመጠበቅ ፡ አቃተው ።
፲፪ ፤ ጀርመኖች ፡ ነገሩ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቶሎ ፡ ተረዱት ። በእስጳንያ ፤ በኢጣልያ ፡
በግሪክም ፡ ሀብት ፡ የመላባቸው ፡ ታላላቅ ፡ ከተሞችና ፡ አያሎች ፡ ያማሩ ፡ መንደሮች ፡
ፍሬ ፡ የመላባቸውም ፡ አገሮች ፡ እንዳሉና ፡ ሮማውያንም ፡ የዓለምን ፡ ሁሉ ፡ ሀብት ፡
የሰበሰቡ ፡ ከነዚሁ ፡ አገሮች ፡ መሆኑን ፡ ተመልከተው ፡ እነዚህ ፡ ተንኰለኞች ፡ የሆኑ ፡
አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ ወደነዚህ ፡ አገሮች ፡ ሄዶ ፡ መኖር ፡ እንዴት ፡ መልካም ፡ ነገር ፡
ይሆን ፡ ብለው ፡ አሰቡ ።
፲፫ ፤ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ እየተዛረፉና ፡ የዕለት ፡ እንጀራቸውን ፡ እንኳ ፡ ለማግኘት ፡ ብዙ ፡
ጣር ፡ በሚያዩበት ፡ አገራቸው ፡ ከመኖር ፡ ይልቅ ፡ መልካሞች ፡ በሆኑ ፡ ቤተ ፡ መን
ግሥቶችና ፡ ቤቶች ፤ ወርቅና ፡ ብር ፡ ፈርጥም ፡ በሞላበት ፡ አገር ፡ መኖር ፡ ምንኛ ፡
መልካም ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አሰቡ ።
፲፬ ፤ ይኸንንም ፡ እንዳሰቡ ፡ ከነርሱ ፡ ተከፍለው ፡ አንዱን ፡ ደፋር ፡ መሪያቸውን ፡
አስቀድመው ፡ ወደ ፡ ጣሊያን ፡ አገር ፡ ተጓዙ ። ቀጥለው ፡ ሌሎቹም ፡ ወዲያው ፡
ተከታተሉዋቸው ። እነዚህ ፡ እንደ ፡ ንብ ፡ የሚርመሰመሱ ፤ መንጎች ፡ የሚመስሉ ፡
ሕዝብ ፡ በጥቂት ፡ ዓመት ፡ በኤውሮጳ ፡ ደቡብ ፡ አውራጃ ፡ ተናኙበት ።
፲፭ ፡ እስከ ፡ አሁንም ፡ በጀርመን ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ዘግይተው ፡ የቀሩ ፡ አያ
ሎች ፡ ናቸው ። እንደዚህ ፡ ሁነው ፡ እየተባዙ ፡ ቄዩና ፡ በሻርለማኝ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡
ሁነው ፡ እጅግም ፡ ኀይል ፡ አግኝተው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በፈረንሳይ ፡ ታሪክ ፡
እንደ ፡ ተረከሁላችሁ ፡ ሻርለማኝ ፡ ተዋግቶ ፡ ድል ፡ አድርጓቸዋል ። እንዲህ ፡ አድ
ርጎ ፡ የጀርመኖች ፡ ጌታ ፡ ከሆነ ፡ ወዲያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፡ እርሱ ፡ ሆነና ፡
መኖሪያውንም ፡ እዚያው ፡ አደረገ ። እንግዲህ ፡ ፈረንሳይንና ፡ ጀርመንን ፡ ሌሎ
ችንም ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ጨምሮ ፡ የርሱ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አገሮች ፡ መሆና
ቸውን ፡ ልብ ፡ አድርጉ ።
፲፮ ፡ የጀርመን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አገር ፡ የተመሠረተው ፡ እንዲህ ፡ ሆኖ ፡ ነው ።
ስለ ፡ ሆነ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሥታት ፡ አገሮች ፡ ተለቅመው ፡ ነው ። እነዚሁም ፡
እያንዳንዱ ፡ የራሳቸው ፡ ገዢዎች ፡ ነበሩዋቸው ። በ፱፻፲፪ ፡ እነዚህ ፡ ገገሮች ፡

ተመኻከላቸው ፡ አንዱን ፡ መርጠው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ማድረግ ፡ የተለመደ ፡ ሆነ ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ እርሱ ፡ የመላው ፡ ጀርመን ፡ በላይ ፡ ሆነ ። እንዲሁ ፡ ጀርመን ፡ በመምረጥ ፡ የሚነግሥ ፡ መንግሥት ፡ ተባለ ። እስከ ፡ ሺ ፡ ፰፻፮ ፡ ዓመት ፡ በዚሁ ፡ ልማድ ፡ ሲገፋ ፡ ቈዩ ።

፲ ፤ በሺ ፡ ፶፮ ፡ አራተኛ ፡ ሄንሪ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሆነ ። ከጳጳስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ፯ኛ ፡ ጋር ፡ የመረረ ፡ ጠብ ፡ ነበረው ። የጳጳስ ፡ ሥልጣን ፡ ያለመጠን ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ አገር ፡ መጥቶ ፡ ይቅርታ ፡ እንዲለ ምን ፡ አስገድዶት ፡ ነበር ።

፩፲ ፤ ሄንሪም ፡ ወደ ፡ ጳጳሱ ፡ መኖሪያ ፡ ፊት ፡ በር ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ አየሩ ፡ አለመጠን ፡ ቀዝቅዞ ፡ ብርዱ ፡ የሚያኰራምት ፡ ነበር ፤ መሬቱም ፡ ሁሉ ፡ በበ ረዶ ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር ። ጳጳስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ በእሳት ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ንጉሡ ፡ መልእክት ፡ ሲልክ ፡ በእግሩ ፡ ጫማ ፡ ሳያገባ ፡ በአፉ ፡ አንዲት ፡ ጕርሻ ፡ ምግብ ፡ ሳይቀምስ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ ከውርጭ ፡ ላይ ፡ ቁሞ ፡ ካልቈየ ፡ አንዲት ፡ ቃል ፡ እንዳይናገረኝ ፡ ብሎ ፡ ላከበት ።

፲፪ ፤ ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ ይህን ፡ ቅጣት ፡ ታግሦ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ባራተኛው ፡ ቀን ፡ ጳጳስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፍታ ፡ አለውና ፡ ሙቀት ፡ አግኝቶ ፡ እህል ፡ እንዲቀምስ ፡ ፈቀደለት ።

፲፫ ፤ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ ከመቶ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የነገሠ ፡ ሄንሪ ፡ የተባለ ፡ ንጉሠ ፡ ነገ ሥት ፡ ኬሌስቲኑስ ፡ ከተባለ ፡ ጳጳስ ፡ ጋር ፡ ተጣልቶ ፡ ነበር ፤ ይቅርታ ፡ ለማግኘት ፡ ተንበርክኮ ፡ የጳጳሱን ፡ ጫማ ፡ እንዲስም ፡ ፈቀደ ። ተጐንብሶ ፡ ሲስም ፡ ከንፈሩ ፡ ጫማውን ፡ ከመንካቱ ፡ ጳጳሱ ፡ እግሩን ፡ አሸሸና ፡ በርግጫ ፡ ቢነዝር ፡ የንጉሡን ፡ ዘውድ ፡ ከራሱ ፡ ላይ ፡ አበረረው ። ዘውዱም ፡ ተሽከርክሮ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ጓዳ ፡ ተን ከባለለ ። የነዚህን ፡ የቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወራሾች ፡ ነን ፡ የሚሉትን ፡ ጠባይና ፡ መን ፈስ ፡ ይህ ፡ ታሪክ ፡ ያሳያችኋል ።

፲፬ በሺ ፡ ፪፻፸፫ ፡ የስዌስርላንድ ፡ ተወላጅ ፡ የሐንስቡርግ ፡ ሩዶልፍ ፡ የጀርመን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እንዲሆን ፡ ተመረጠ ። እርሱም ፡ የዛሬዎቹ ፡ የአስትሪያ ፡ ነገሥ ታት ፡ አባት ፡ ነው ፡ እርሱ ፡ ከነገሠ ፡ ወዲህ ፡ በጀርመን ፡ ከነገሡት ፡ የሚበ ዙት የርሱ ፡ ዘሮች ፡ ናቸው ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ጀርመን ፡ በጥንት ፡ ዘመን ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሕዝብ ፡ ኖሮዋል ፡ ? ስለ ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ ጥቂት ፡ ተናገር ።

፪ ፤ ጥንት ፡ ዘመን ፡ እንዴት ፡ ነበሩ ፡ ? በቄሣር ፡ ዘመን ፡ እንዴት ፡ ኖረዋል ፡

፫ ፤ የሮማውያን ፡ ጥበብ ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ? የባለጉ ፡ ሕዝብ ፡ እንደምን ፡ ሠለጠኑ ፡ ? ምን ፡ አደረጉ ፡ ?

፬ ፤ ከቄሣር ፡ በኋላ ፡ አያል ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ሲኖሩ ፡ ሮማውያን ፡ እንደ ምን ፡ ኑረዋል ፡ ?

፭ ፤ ጀርመኖች ፡ ቶሎ ፡ ብለው ፡ ምን ፡ አገኙ ፡ ?

፮ ፤ ምን ፡ አሰቡ ፡ ?

፯ ፤ እኩሌቶቹ ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ? በጥቂት ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ምንና ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?

፰ ፤ በጀርመን ፡ አገር ፡ የቀሩት ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ? ሻርለማኝ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? መንግሥቱ ፡ ምን ፡ ጨመረ ፡ ?

፱ ፤ የጀርመን ፡ መንግሥታት ፡ እንደምን ፡ ናቸው ፡ ? በ፱፻፲፪ ፡ ምን ፡ ልማድ ፡ አደረጉ ፡ ?
ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ?

፲ ፤ ሄንሪ ፡ ፬ኛ ፡ ቄሣር ፡ የሆነው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? ጳጳስ ፡ እንዴት ፡ አደረገ ፡ ?

፲፩ ፤ ጳጳሱ ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ቅጣት ፡ ጫነበት ፡ ?

፲፪ ፤ ስለ ፡ ሄንሪና ፡ ስለ ፡ ጳጳስ ፡ ሴሊስቲኑስ ፡ አጭር ፡ ታሪክ ፡ ተናገር ።

፲፫ ፤ በ፲፱፻፴፫ ፡ የጀርመን ፡ ንጉሥ ፡ ማን ፡ ነበር ፡ ? ስለሱ ፡ ምን ፡ ይነገራል ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፴፯ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፡ ስዊስርላንድ ።

፩ ፤ እስከ ፡ ሺ፡፫፻-፯ ፡ ድረስ ፡ ስዊስርላንድ ፡ በጀርመን ፡ መንግሥት ፡ ስትገዛ ፡ ኑራለች ፤ ስዊስርላንድ ፡ እንደምታውቁት ፡ በጀርመን ፡ በፈረንሳይና ፡ በጣሊያን ፡ የተከበበች ፡ ተራራ ፡ የበዛባት ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ አገር ፡ ናት ።

፪ ፤ መጽሐፌን ፡ ለሚያነቡ ፡ ጐበዛዝት ፡ ብዙ ፡ ምኞት ፡ ስላለኝ ፡ ስዊስርላንድን ፡ ወደፊት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሳያዩዋት ፡ አይቀሩም ፡ በማለት ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ። ወደዚያ ፡ የሄዳችሁ ፡ እንደሆን ፡ መልካም ፡ መንገድ ፡ ታገኛላችሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ በእግራችሁ ፡ እንድትሄዱ ፡ እመክራችኋለሁ ፤ ብዙ ፡ የሚታዩ ፡ መልካም ፡ ነገሮች ፡ አሉ ። እስከ ፡ ሰማይ ፡ ደርሰው ፡ ደመና ፡ መስለው ፡ የሚታዩ ፡ ተራሮች ፡ አሉ ። እንዲሁም ፡ ዙሪያቸውን ፡ በተራራ ፡ የተከበቡ ፡ ሰማይ ፡ የሚመስሉ ፡ አያሎች ፡ ባሕሮች ፡ መስተዋት ፡ መስለው ፡ ይታያሉ ። ደግሞም ፡ ለምለም ፡ የሆኑ ፡ ጐድጓዳ ፡ አገሮችና ፡ የጥንት ፡ የከተማ ፡ ፍራሾች ፡ ይታያሉ ። የሚያስደንቋችሁን ፡ ነገሮች ፡ ለማየት ፡ ስትሉ ፡ በየደቂቃው ፡ መቆማችሁ ፡ የማይቀር ፡ ነውና ፡ ጋሪ ፡ ወይም ፡ ሠረገላ ፡ የያዛችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያስቸግራችኋል ፡ ስለ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፫ ፤ አገሪቱ ፡ ስዊስርላንድ ፡ አንዲት ፡ ትንሽ ፡ ዓለም ፡ ሆና ፡ ሳለች ፡ በዚያ ፡ ነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ልውጥ ፡ ሆኖ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ ከተራራ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ በማይታይበት ፡ አገር ፡ እንደ ፡ አውሬ ፡ ተናዳጅ ፡ የሆኑ ፡ ሕዝብ ፡

ይገናኙናል ፣ ብላችሁ ፣ ታስቡ ፣ ይሆናል ። ይሁን ፣ እንጂ ፣ ስዊሶች ፣ ጨዎችና ፣ ቁምነገረኞች ፣ ናቸው ፤ ሰውነቴና ፣ ቀላጥሚ ፣ አረጀና፣አቀበትና ፣ ቍልቍለቱን፣ መውረድና ፣ መውጣቱ ፣ ባያቅተኝ ፣ ስዊስርላንድን ፣ ሄጄ ፣ ብጐበኘው ፣ ምንኛ ፣ በወደድሁ ፣ ነበር ።

፬ ፤ አሁንም ፣ ስለ ፣ ስዊስርላንድ ፣ አጭር ፣ ታርክ ፣ እጨምራለሁ ። አልቤርት ፣ አንደኛ ፣ በነገሠ ፣ ጊዜ፣በሺ፣፪፻፺፰ ፣ በስዊስርላንድ ፣ ላይ ፣ እንደግፈኛ፣ሆኖ፣ገዛ ፤ ከርሱ የከፉትን ፣ ግፈኞች ፣ ሹሞችንም ፣ ሾመ ። ከነዚህም ፣ አንዱ ፣ ጌስለር ፣ ይባል ፣ ነበር ። ቆቡን ፣ በረጅም ፣ ሽመል ፣ ጫፍ ፣ ሰቀለና ፣ ሰው፣ሁሉ ፣ ለቆቡ፣ እየተጐነበሰ ፣ እጅ ፣ እንዲነሣ ፣ አዘዘ ።

፭ ፤ አንድ ፣ ዊልየም ፣ ቴል ፣ የተባለ ፣ ስመ ፣ ጥሩ ፣ ገበሬ ፣ ለጌስለር ፣ ቆብ ፣ እጅ ፣ አልነሣም ፤ አልጐነበስም ፣ ብሎ ፣ ሞገደ ። መጽሐፌን ፣ የምታነቡ ፣ ታሪኩን ፣ ሳትሰሙ፣አትቀሩም ። ጌስለር፣አንዲት ፣ የአፕል ፣ ፍሬ ፣ በቴል ፣ ልጅ ፣ ራስ፣ ላይ፣ አድርጎ ፣ የአፕሊቱን ፣ ፍሬ ፣ በጠመንጃ ፣ ተኵሶ፣እንዲመታ ፣ አዘዘው ። ቴል ፣ እን ደታዘዘው ፣ ጠመንጃ ፣ አንሥቶ ፣ አነጣጥሮ ፣ ቢተኵስ ፣ ልጁን፣አንድ፣ጕዳት ፣ ሳያገ ኘው ፣ የአፕሊቱን ፣ ፍሬ ፣ ከልጁ ፣ ራስ ፣ ላይ ፣ አበረራት ።

፮ ፤ ስዊሶች ፣ በጀርመን ፣ ንጉሠ ፣ ነገሥት ፣ ላይ ፣ በሸፈቱ ፣ ጊዜ፣ዋና፣መሪያቸው፣ ቴል ፣ ነበር ። ከጀርመን ፣ ንጉሥ ፣ ጦር ፣ ጋር ፣ ስድሳ ፣ ጊዜ ፣ ከተጋጩ ፣ በኋላ ፣ የስዊስርላንድ ፣ ነጻነት ፣ ተመሥርቶ ፣ ቀረ ። ከዚያ፣ ወዲህ ፤ ስዊስ ፣ ነጻነት ፣ ያለ ውና ፣ በራሱ ፣ አዳሪ ፣ የሆነ ፣ የሬፑብሊክ ፣ መንግሥት ፣ ተብሎ ፣ ቀረ ።

፯ ፤ ከስዊስርላንድ ፣ ሰዎች ፣ አንዳንዶቹ ፣ በምድር ፣ ላይ ፣ ከታየ፣ምንም፣አምስት ፣ መቶ ፣ ዓመት ፣ ቢሆን ፣ ዊሊየም ፣ ቴል ፣ አለ ፣ አልሞተም ፣ ብለው ፣ ያምናሉ ፣ ይባላል ። ሬፑብሊኩን ፣ ሲመሠርቱ ፣ ካረዱት ፣ ከሁለቱ ፣ ሽማግሌዎች ፣ ጋር ፣ በሉ ሴርን ፣ ባሕር ፣ አጠገብ ፣ ባለው ፣ ዋሻ ፣ ውስጥ ፣ እንቅልፍ፣እንደ፣ ወሰደው ፣ ይመ ስላቸዋል ።

፰ ፤ እነዚህ ፣ ሦስቱ ፣ እንቅልፍ ፣ የገረዘዛቸው ፣ የማጕረምረም ፣ (የማንኳረፍ ፣) ሰዎች ፣ ይባላሉ ። ስዊስርላንድ ፣ ነጻነቱዋን ፣ ባጣች ፣ ቍጥር ፣ በጣም ፣ የሚያ ሥቅ ፣ ነገር ፣ ይደረጋል ። እነዚህ ፣ ሦስቱ ፣ ከእንቅልፋቸው ፣ መንቃት ፣ ይጀም ራሉ ። ከጥንት ፣ ልብሳቸውና ፣ መሣሪያቸው ፣ ጋር ፣ ይወጣሉ ። ነጻነታቸውን ፣ ለመጠበቅ ፣ እንዲዋጉ ፣ ሕዝቡን ፣ ያስነሣሉ ፣ ይባላል ።

፱ ፤ በሺ፣፫፻፺፬ ፣ ከሞተው ፣ ከዊልየም ፣ ቴል ፣ ወዲህ፣መቸውንም፣ ስዊስርላንድ፣ ነጻነቷን ፣ ጠብቃ ፣ ትኖራለች ። በፈረንሳይ ፣ ዐመፅ ፣ ጊዜ ፣ ተሸንፋ ፣ ነበር ። እን ደ፣ገናም፣ነጻነቷን ፣ አግኝታ ፣ ኖረች ፤ ይሁን ፣ እንጂ ፣ በዙሪያዋ ፣ ባሉት፣ አገሮች፣ የነገሡት ፣ ሕዝብዋን ፣ እየተጫኑ ፣ ያስቸግሩ ነበር ።

፲ ፤ አያሎች ፣ ስዊሶች ፣ በሌላ፣አገር ፣ ጌትነት ፣ እናገኝ፣እንደ፣ሆነ፣እንፈትን፣እያሉ ፣ ከገራቸው ፣ ወጥተው ፣ ይሄዳሉ ። አኩሉ ፣ ወታደርነት ፤ እያሉ ፣ ወደጦርነት ፣ ይገ

ባሉ ። እኩሌቶቹም ፣ ለዘፈንና ፣ ለመታየት ፣ እያሉ ፣ ወደ ፣ ፈረንሳይና ፣ ወደ ፣ እንግሊዝ ፣ ለን
ድን ፣ እየሄዱ ፣ ትንሽ ፣ ገንዘብ ፣ ያገኛሉ ።

፲፩ መቸውንም ፣ በነዚህ ፣ ታላላቅ ፣ ከተሞች ፣ የስዊስ ፣ ልጅ ፣ በመንገድ ፣ ላይ ፣ ለለት ፣ ምግቡ ፣ ትንሽ ፣ ገንዘብ ፣ ሲለምን ፣ ታገኙታላችሁ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ የስዊስርላንድ ፣ መንግሥት ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?
ስዊስርላንድ ፣ ወዴት ፣ ነው ፣ ?
፪ ፤ ያገሩን ፣ መልክ ፣ ተናገር ።
፫ ፤ ሕዝቡ ፣ እንዴት ፣ ናቸው ፣ ?
፬ ፤ አልቤርት ፣ አንደኛ ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ? ጌስለር ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ?
፭ ፤ ዊሊየም ፣ ቴል ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ?
፮ ፤ ስዊስርላንድ ፣ ነጻነቱዋን ፣ እንደምን ፣ አገኘች ፣ ?
፯ ፤ ስለ ፣ ዊሊየም ፣ ቴልና ፣ ስለ ፣ ሁለቱ ፣ ጓደኞች ፣ ምን ፣ ይነገርላቸዋል ፣ ?
፰ ፤ ቴል ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ሞተ ፣ ? ከቴል ፣ ወዲህ ፣ ስዊስርላንድ ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ?
፲ ፤ የስዊስ ፣ ሕዝብ ፣ ሁኔታ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?

## ምዕራፍ ፣ ፻፵፯ ፣ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፣ ጀርመን ፣ ታሪክ ፣ መከናወን ።

፩ ፤ አሁንም ፣ የጀርመንን ፣ ታሪክ ፣ እነግራችኋለሁ ። ሻርል ፣ አምስተኛ ፣ እጅግ ፣ የታወቀ ፣ የጀርመን ፣ ንጉሠ ፣ ነገሥት ፣ ነበር ፤ እንዲሁም ፣ እርሱ ፣ የእስጳንያ ፣ ንጉሥ ፣ ሳለ ፣ የኔዝርላንድና ፣ የኢጣሊያ ፣ ገዢ ፣ ነበር ።

፪ ፤ ይህ ፣ ታላቅ ፣ ንጉሥ ፣ ፸፬ ፣ ዓመት ፣ በሆነው ፣ ጊዜ ፣ ጉልበቱ ፣ እየደከመ ፤ ኀይሉ ፣ እየተቀነሰ ፣ መሄዱን ፣ ዐውቆ ፣ ስለዚህ ፣ ዘውዱን ፣ አውልቆ ፣ ለልጁ ፣ ለፊልጶ ፣ ሰጠና ፣ እስጳንያ ፣ ውስጥ ፣ ኤስትሬማድራ ፣ በተባለች ፣ ገዳም ፣ ሄዶ ፣ ተቀመጠና ፣ ያልባሌ ፣ ልብስ ፣ እየለበሰ ፣ በጸሎት ፣ ተጠምዶ ፣ ያታክልት ፣ ሥራ ፣ እየሠራ ፣ ኖረ ።

፫ ፤ አንድ ፣ ቀን ፣ ሰውነቱን ፣ በመግነዝ ፣ ጠቀለለና ፣ በሚቀበርበት ፣ ሣጥን ፣ ገብቶ ፣ እንደ ፣ ሞተ ፣ መስሎ ፣ ተጋደመ ። ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ተሸክመው ፣ ወደ ፣ መቃብር ፣ ስፍራ ፣ እንዲወስዱት ፣ አሽከሮቹን ፣ አዘዘ ። አንባቢዎች ፣ ሆይ ፣ ንጉሡ ፣ በሕይወቱ ፣ እን ዲቀብሩት ፣ ማለቱ ፣ አይምሰላችሁ ፣ ነገር ፣ ግን ፣ ሕይወቱ ፣ በቅርብ ፣ ጊዜ ፣ እንዲፈ ጸም ፣ ራሱን ፣ ለማሳሰብ ፣ ስለ ፣ ፈለገ ፣ ነው ። የዚሁ ፣ አደራረግ ፣ ፍታቱና ፣ ሥርዓቱ ፣ የሕይወቱን ፣ መጨረሻ ፣ አቃረበውና ፣ በሰውነቱ ፣ ትኩሳት ፣ ተሰማው ፤ በዚሁ ፣ ምክንያት ፣ በሺ ፣ ፭፻፶፰ ፣ ሞተ ።

፬ ፤ በሺ፮፻፲፱ ፡ የነገሠ ፡ ፈርዲናንድ ፡ ሁለተኛ ፡ የተባለው ፡ ንጉሥ ፡ በጀርመን ፡ አገር ፡ የሚኖሩትን ፡ የፕሮቴስታንቶችን ፡ ሕዝብ ፡ የመረረ ፡ አሳዳጅ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ካቶሊኮች ፡ ሐዋርያው ፡ ንጉሥ ፡ ይሉት ፡ ነበር ፤ በርሱው ፡ ጭከና ፡ የተነሣ ፡ ጉስታፉስ ፡ አዶልፉስ ፡ የተባለውን ፡ የስዊድንን ፡ ንጉሥ ፡ ርዳታ ፡ እንዲለምኑ ፡ አስደረጋቸው ። ይህም ፡ እንዲሁ ፡ ወደ ፡ ጀርመን ፡ አገር ፡ ተሻገረና ፡ አገሪቱን ፡ ወረራት ፤ በመጨረሻውም ፡ ተዋግቶ ፡ አያል ፡ ጊዜ ፡ ድል ፡ አድርጓል ።

፭ ፤ አንባቢዎቹ ፡ ለማወቅ ፡ እንደሚመኙት ፡ ያለ ፡ ጉድና ፡ ድንቅ ፡ የመላበት ፡ ታሪክ ፤ በጀርመን ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ አይገኝም ። ጥቂቶቹ ፡ ወይም ፡ ሁሉም ፡ ቢሆኑ ፡ የቀድሞ ፡ የጀርመን ፡ ነገሥታት ፡ የሠሩት ፡ እጅግ ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ የለም ። አያሎች ፡ ገዦች ፡ ከደረጉት ፡ በደል ፡ እነዚያ ፡ ንጹሓን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ይታያሉ ።

፮ ፤ ከላይ ፡ እንደ ፡ ተናገርሁ ፡ መቸውንም ፡ የጀርመን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የሚሆነው ፡ ከሀፕስቡርግ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ ፕሪንስ ፡ ነው ። የአስትሪያ ፡ ግዛት ፡ በተከናወነላቸው ፡ ነገሥታት ፡ እየሰፋ ፡ ሄደና ፡ በኋላ ፡ ታላቅና ፡ ኀይለኛ ፡ ለመሆን ፡ ቦቃ ።

፯ ፤ አሁን ፡ ብቻውን ፡ ለመዋጋት ፡ ይችላል ። በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጊዜ ፡ ከቱርክ ፤ ከፈረንሳይና ፡ ከእስጳንያ ፤ ከፕሩስያም ፤ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ከሌሎች ፡ ከጀርመን ፡ ነገሥታት ፡ ጋር ፡ ታግሏል ።

፰ ፤ በሺ፡፯፻፺፪ ፡ ሁለተኛ ፡ ፍራንሲስ ፡ የተባለ ፡ የጀርመን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሆነ ። ከናፖሊዮን ፡ በናፓርት ፡ ጋር ፡ ጦርነት ፡ ጀመረና ፡ የርሱ ፡ ጦር ፡ ድል ፡ ሆነ ። ወዲያው ፡ በሺ፡፰፻፮ ፡ የጀርመን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መባሉን ፡ እንዲለቅ ፡ ግድ ፡ ሆነበት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የአስትሪያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሆነ ፤ እርሱ ፡ በሞተበት ፡ ዘመን ፡ በሺ፡፰፻፲፭ ፡ ከኤውሮጳውያን ፡ ኀያላን ፡ መንግሥታት ፡ አንዱ ፡ ኀይለኛው ፡ የታወቀው ፡ መንግሥት ፡ የርሱ ፡ መንግሥት ፡ ነበር ።

፱ ፤ በፕሩሲያ ፡ ንጉሥ ፡ በዊሊየም ፡ አንደኛ ፡ መሪነት ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ የጀርመን ፡ ጦር ፡ ምሳሌ ፡ ከሌለው ፡ ማከናወን ፡ የተነሣ ፡ በሺ፡፰፻፸—፸፩ ፡ የጀርመን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ማዕርግ ፡ ተሰጠውና ፡ ተቀበለ ። ስምምነት ፡ የነበራቸው ፡ የጀርመን ፡ መንግሥታትም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አንድ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ሆኑ ።

<u>ጥያቄ ።</u>

፩ ፤ ቻርልስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፪ ፤ ስለርሱ ፡ አጭር ፡ ታሪክ ፡ ተናገር ።

፫—፬ ፤ ቻርልስ ፡ ፮ኛ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ፡ ? ፈርዲናንድ ፡ ፪ኛ ፡ የተባለ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ መንገሥ ፡ ጀመረ ፡ ? እርሱ ፡ እንደምን ፡ ሆነ ፡ ?

ፕሮቴስታንቶች ፡ እንዲያደርጉት ፡ ያስገደዷቸው ፡ ምንድነው ፡ ?

፮ ፤ የጀርመን ፡ የኋለኛው ፡ ንጉሥ ፡ ማነው ፡ ?

የጀርመን ፡ ቄሣር ፡ እንደምን ፡ ሆነ ፡ ? የኦስትሪያ ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፯ ፡ ኦስትሪያ ፡ ለጦርነት ፡ የተወራረደው ፡ ከየትኛው ፡ አገር ፡ ጋር ፡ ነው ፡ ?

፰ ፡ በ፲፯፻፺፱ ፡ የጀርመን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ማን ፡ ሆነ ፡ ? በ፲፰፻—፮ ፡ ምን ተደረገ ፡ ?

፱ ፤ የጀርመን ፡ ቄሣር ፡ የሆነው ፡ ማነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፻፵፫ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፡ ኦስትሪያና ፡ ስለ ፡ ሁንጋሪየ ።

፩ ፤ አስትሪያ ፡ አንድ ፡ ሰፊ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ነው ። በደቡብ ፡ ከረሺያ ፤ በሰሜን ፡ ከአድሪያቲክ ፡ ባሕርና ፡ ከሴርብያ ፡ ይዋሰናል ። በምዕራብም ፡ ከጀርመን ፡ አገሮችና ፡ ከስዊስላንድ ፡ ከኢጣሊያም ፡ ይዋሰናል ።

፪ ፤ ይህ ፡ አገር ፡ የተባበሩ ፡ የጀርመን ፡ መንግሥታት ፡ ለተባሉት ፡ ረጅም ፡ ዘመናት ፡ ዋና ፡ መሪ ፡ ሆኖ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ ተለይቷል ። በሺ ፡ ፲፰፻፷፮ ፡ ጦርነት ፡ ተደርጎ ፡ ፕሩሲያ ፡ ለጀርመን ፤ ቬኒስም ፡ ለጣልያን ፡ እንዲሆን ፡ ተደረገና ፡ ተስማሙ ። የአስትሪያን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አገር ፡ የተከፋፈሉ ፡ ፲፯ ፡ አህጉር ፡ ናቸው ። የሕዝቡ ፡ ቍጥር ፡ ፴፭ ፡ ሚሊዮን ፡ ይሆናሉ ። የመንግሥቱ ፡ ሃይማኖት ፡ የሮም ፡ ካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የግሪክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይከበራል ፤ ሌሎችም ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሁሉ ፡ አይነቀፉም ።

፫ ፤ በጀርመን ፡ ክፍል ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ የአስትሪያ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ቬና ፡ ይባላል ። ይህም ፡ እጅግ ፡ ከሚያምሩት ፡ ከኤውሮጳ ፡ ከተሞች ፡ አንዱ ፡ ነው ። የተሠራውም ፡ ዳኑብ ፡ ከተባለው ፡ ከታላቁ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ነው ። በክረምት ፡ በረዶ ፡ ይሆናል ፤ ሕዝቡ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መንኰራኵሮችና ፡ መንሸራተቻዎች ፡ እየተሽከረከሩና ፡ እየተንሸራተቱ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። እንዲህ ፡ ሲያደርጉ ፡ ማየት ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ።

፬ ፤ በቬና ፡ ከተማ ፡ ጕልተው ፡ የሚታዩ ፡ አያሌ ፡ ቤቶች ፡ አሉ ። ከነዚህም ፡ ዋነኞቹ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፤ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ያለበት ፡ ቤት ፤ ገንዘብ ፡ የሚቀረጽበት ፡ ቤትና ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ናቸው ። ይህም ፡ የመጻሕፍት ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ የሚገኙበት ፡ ስለሆነ ፤ የውጪ ፡ እንግዶች ፡ እየመጡ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያዩታል ። በዚህም ፡ ሙዜውም ፡ በኤውሮጳ ፡ ከሚታየው ፡ ይልቅ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሚታይ ፡ ነገር ፡ መልቶበታል ። የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አገሮች ፡ ከሚባሉ ፡ ሁሉ ፡ አብልጦ ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራበት ፡ በቤና ፡ ነው ።

፭ ፤ በጀርመን ፡ ክፍል ፡ ያለው ፡ አስትሪያ ፡ ከዚሁም ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ወገን ፡ ያለው ፡ ክፍል ፡ ባላገሮቹ ፡ የጀርመን ፡ ቋንቋ ፡ ይናገራሉ ። ልማዳቸውና ፡ ጠባያቸው ፡ ፍጹም ፡ የጀርመን ፡ ነው ። የዚህ ፡ አገር ፡ ታሪክ ፡ የተነገረው ፡ ከብዙ ፡ በከፍሉ ፡ ነው ። ጥንት ፡ አገሩን ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ ይኖርበት ፡ ነበር ፤ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ ከጀርመን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አገሮች ፡ አንደኛው ፡ አገር ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ መንግሥት ፡ ሆነና ፡ የአስትሪያ ፡ መንግሥት ፡ ለመባል ፡ በቃ ።

፮ ፤ በዚህ ፡ ዘመን ፡ አርቺዱኪ ፡ ይባላል ። ይህም ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዜጋ ፡ በሆኑ ፡ ባንድ ፡ አርቺዱክ ፡ ይገዛል ። በሺ ፡ ፲፪፻፸፫ ፡ ሩዶልፍ ፡ ከሀጵስቡርግ ፡ የን

ጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ መንግሥት ፡ ወረሰ ። እንደነገርኋችሁ፡ የአስትሪያ ፡ ነገሥታት፡ ከርሱ ፡ ተያይዘው ፡ የመጡ ፡ ናቸው ። ከርሱ ፡ በኋላ ፡ አስትሪያ፡ኀይሉ፡በፍጥነት፡ እየደከመ ፡ ሄደ ። የርሱም ፡ ገዢ ፡ እያደር ፡ የመላው ፡ ጀርመን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት፡ ነበር ፡ ተብሎ ፡ ይታሰባል ።

፮ ፤ ብዙ ፡ ጦርነት ፡ አድርጓል ፤ ይልቁንም ፡ ከስዊድን ፤ ከፈረንሳይ ፤ ከቱርክ ፡ ጋር ፡ ተዋግቶአል ። በሺ፡፮፻፹፫ ፡ ቱርኮች ፡ እየገፉ ፡ ከመኻከሉ ፡ ድረስ ፡ ክንዳ ቸውን ፡ ዘርግተውበት ፡ ከተማዪቱ ፡ ቬና ፡ ሳትቀር ፡ ዙሪያዋን ፡ ከበዋት ፡ ነበር፤ ነገር ፡ ግን ፡ በመጨረሻው ፡ ቱርኮችን ፡ ተመኻከል ፤ እየነዱ ፡ አስወጥዋቸው ።

፯ ፤ የሚችሉ ፡ ጄኔራሎችና ፡ የተሰናዳ ፡ ጦር ፡ ስለ፡ነበረው፡በሺ፡፰፻፱ ፡ አስትሪያ ከቦናፓርት ፡ ጋር ፡ ጦርነት ፡ አነሣ ። ነገር ፡ ግን ፡ የፈረንሳይ ፡ ንጉሥ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ድል ፡ አደረጋቸውና ፡ በመጨረሻው ፡ ቬና ፡ ወደ፡ተባለው ፡ ከተማቸው ፡ ገባ ። በዚህም ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጋር ፡ ዕርቅ ፡ አደረገ ፤ ዳሩ ፡ ግን፡ከግዛቱ ፡ ቅምጥል ፡ አድርጎ ፡ አያል ፡ አገር ፡ ወሰደበት ፤ ዜጎቹ ፡ አልበቃንም ፡ እያሉ ፡ በኋለኛው ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ጭቅጭቅ ፡ ነበር ።

፰ ፤ በሺ፡፰፻፵፰ ፡ የተደረገው ፡ ጦርነት ፡ ለአስትሪያ ፡ ሕዝብ ፡ ዕዳ ፡ ጨመረ ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ፡ ግን ፡ ላገሩ ፡ ልማትና ፡ እድገት ፡ የሚያስብ ፡ ይመስል ፡ ነበር ። በሺ፡፰፻፵፰ የአስትሪያ፡ግዛት ፡ እጅግ ፡ ተስፋፍቶ ፡ ነበር ። በሺ፡፰፻፶፱ ፡ ሎምባርዲ ፡ ከተባለው ፡ አውራጃ ፡ የሚበልጠው ፡ ክፍል ፡ ለኢጣሊያ ፡ ተሰጠ፤ በሺ፡፰፻፷፮፡ ከሎምባርዲ ቀርቶ ፡ የነበረውን ፡ ለዚሁ ፡ መንግሥት ፡ ተጨመረለት ፡ ይህም ፡ ከአስትሪያ ፡ መንግሥት ፡ ተከፍሎ ፡ የተወሰደው ፡ በእንግሊዝ ፡ መሥፈሪያ፡ ፲፮ሺ፡፩፻ ፡ እስ ኩዌር ፡ ማይል ፡ ነው ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ አስትሪያ ፡ ያለው ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ ? ዳርቻው ፡ እስከ ፡ የት ፡ ይደርሳል ፤ ?

፪ ፤ በ፲፮፻፹፫ ፡ በተደረገው ፡ ጦርነት ፡ ምን ፡ ጥቅም ፡ ተገኘ ፡ ?

፫ ፤ ቬና ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ዳኑብ ፡ ምንድነው፡? ምን ፡ ጨዋታ ፡ ይደረጋል ፡ ?

፬ ፤ ስለ፡ዋናው፡የሕዝብ ፡ አዳራሽ ፡ ተናገር ።

፭ ፤ በአውስትርያ ፡ ያለው ፡ የጀርመን ፡ ክፍል ፡ የቱ ፡ ነው ፡ ? ጥንት ፡ ምን፡ ይባል ፡ ነበር ፡ ?

፮ ፤ በኋላ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ? በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ይባላል ፡ ? በ፲፪፻፸፫፡ዙፋ ኑን ፡ ማን ፡ ወረሰ ፡ ?

አውስትሪያና ፡ አርቺዱክ ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?

፯ ፤ የአውስትርያ ፡ ጦርነት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

በ፲፮፻፹፫ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?

፰ ፤ በ፲፰፻ ፱ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ? ቦናፓርት ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፱ ፡ ዛሬ ፡ የአውስትሪያ ፡ ስፋት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይታሰባል ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፻፵፱ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ሁንጋርያና ፡ በሄሚያ ፡ ስለቴሮል ፡ (ታይሮል ። )

፩ ፤ አስትሪያ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ አሉት ፡ አገሮች ፡ ጥቂት ፡ አሳብ ፡ እሰጣችኋለሁ ፡ ሁን ጋሪ ፡ አያሎች ፡ አውራጃዎችን ፡ ጨምሮ ፡ ሰፊ ፡ አገር ፡ ነው ፤ ዋና ፡ ከተማው ቡዳ ፡ ይባላል ፡ የተሠራውም ፡ ዳኑብ ፡ በሚሉት ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡ ነው ።

፪ ፤ ሁንጋሪያ ፡ አየሩ ፡ ለመኖሪያ ፡ የተስማማ ፡ ነው ። ወይን ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ያንዠረግጋል ። ጥሩ ፡ ነቢት ፡ የሚሠራው ፡ ከዚሁ ፡ ነው ። በየተራራው ፡ ላይ ፡ የሚበቃ ፡ ወርቅ ፡ ይገኛል ። ባላገሮቹ ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ ናቸው ። እነዚህም ሀብታሞችና ፡ ድሆች ፡ ናቸው ። ሀብታሞቹ ፡ በጥሩ ፡ እልፍኝ ፡ ይኖራሉ ፤ ድሆቹ ፡ ግን ፡ ከባሮቻቸው ፡ የሚሻሉት ፡ ጥቂት ፡ ነው ።

፫ ፤ ከጥንቱ ፡ የሁንጋሪያ ፡ ባላገሮች ፡ አያሎቹ ፡ ቊጡዎችና ፡ ተናዳጆች ፡ ነገዶች ፡ አሉባቸው ። ጥንት ፡ ዘመን ፡ ከእስያ ፡ ፈልሰው ፡ አልታይ ፡ የሚሉትን ፡ ተራራ ፡ ዙረው ፡ ወደ ፡ ኤውሮጳ ፡ የመጡ ፡ ይመስላሉ ። ምናልባት ፡ እነዚህ ፡ ታርታር ፡ የተባሉት ፡ ነገድ ፡ ሳይሆኑ ፡ አይቀሩም ፤ ቱርኮች ፡ ይባላሉ ። እነዚም የሳራሴንን ፡ መንግሥት ፡ ገልብጠው ፡ የራሳቸውን ፡ የቱርክን ፡ መንግሥት ፡ የመሠረቱ ፡ ፯ ናቸው ።

፬ ፤ ዋኖቹ ፡ የሁንጋሪያ ፡ ነገዶች ፡ ግን ፡ ሁንስ ፡ ይባላሉ ። ልብ ፡ ታደርጉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ደሙ ፡ የፈላበት ፡ አቲላ ፡ የተባለ ፡ በ፬፻፶፫ ፡ ከነዚሁ ፡ አንድ ፡ የጦር ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ ጣሊያን ፡ አገር ፤ ወስዶ ፡ ነበር ። አስቀድሞ ፡ ብዙ ፡ ጦርነት ፡ ተዋግቶ ፡ የግሪክን መንግሥት ፡ አስገብሮታል ። በኋላም ፡ አልፐን ፡ ተሻግሮ ፡ በጣሊያን ፡ ሜዳ ፡ ሰው ፡ በሌለበት ፡ በጠፉ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ በባላገሩ ፡ መኻከል ፡ ተንጣለለበት ፤ ከተማዪቱንም ፡ ሮምን ፡ ተቃርበዋት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዲመለስ ፡ ግድ ፡ ሆነበትና ፡ ወዲያው ፡ በ፬፻፶፮ ፡ ሞተ ።

፭ ፤ ሁንጋሪ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ አዘውትሮ ፡ የሚታይ ፡ ጦርነት ፡ ነበረው ። በሺ ፡ ፭፻፳፮ ፡ እስከ ፡ ሞተው ፡ እስከ ፡ እስቴፍን ፡ ድረስ ፡ የአገሩ ፡ አገዛዝ ፡ የንጉሥ ፡ ማዕርግ ፡ አላስፈለገውም ። በሺ ፡ ፮፻፹፫ ፡ ሁንጋሪ ፡ የአስትሪያ ፡ መንግሥት ፡ ክፍል ፡ ሆነ ። የአስትሪያም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሰኔ ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ሺ ፡ ፰፻፷፯ ፡ የሁንጋሪያ ፡ ንጉሥ ተባለ ።

፮ ፤ በሄሚያ ፡ በተራሮች ፡ የተከበበ ፡ አገር ፡ ነው ። አራት ፡ ሚሊዮን ፡ ባላገሮች ፡ አሉበት ፡ የብር ፡ ጕድጓድ ፡ ቆርቆሮ ፤ የከበረ ፡ ደንጊያ ፡ መልቶበታል ። ዛሬ ፡ ካሉት ፡ ሕዝብ ፡ አያሎቹ ፡ አይሁድ ፡ ናቸው ። ደግሞ ፡ አያሎች ፡ የሚያስገርሙ ፡ ዘዋሪዎች ፡ ጊቢሲስ ፡ የሚባሉ ፡ ሕዝብ ፡ አሉበት ።

፯ ፤ የዚህ ፡ አገር ፡ ስም ፡ የተገኘው ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፬፻ ፡ ዓመት ፡ በዚያ ፡ ይኖሩ ፡ ከነበሩ ፡ በእስያ ፡ ኬልትስ ፡ ከሚባሉ ፡ ነገድ ፡ ነው ። ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡

፬፻-፺ ዓመት ፡ በዱክ ፡ የሚገዙ ፡ ጀርመኖች ፡ በዚያ ፡ ነበሩና ፡ ኪልቶችን ፡ ከዚያ ፡ አስ ወጥተው ፡ እንዳባረሩዋቸው ፡ ይታያል ። ሻርለማኝ ፡ አገሩን ፡ የርሱ ፡ ግዛት ፡ ክፍል ፡ አድርጎት ፡ ነበር ። በኋላ ፡ የንጉሥ ፡ መንግሥት ፡ ሆነ ። በሺ፡፰፻፮ ፡ የአስትሪያ ፡ ገንዘብ ፡ ሆነና ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እንደዚሁ ፡ ሆኖ ፡ ቀረ ።

፰ ፤ ስለ ፡ ኦስትሪያ ፡ ያገር ፡ ክፍሎችና ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ስለሚገዙት ፡ አገ ሮች ፡ ከዚህ ፡ አብልጬ ፡ ልነግራችሁ ፡ አያስፈልገኝም ። ስለ ፡ ቬኒስ ፡ አያል ፡ አሳብ ፡ አሳይቻለሁ ። ስፍራ ፡ ባገኝ ፡ ስለ ፡ ጀግናዪቱ ፡ ስለ ፡ ታይሮሊስ ፡ በነገር ኳችሁ ። ይህችም ፡ በጀርመንና ፡ በኢጣሊያ ፡ መኻከል ፡ ባለው ፡ ተራራና ፡ ለኦስ ትሪያ ፡ በሚገዙ ፡ በሌሎች ፡ ነገዶች ፡ መኻከል ፡ ያለች ፡ አገር ፡ ናት ።

፱ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ታሪክ ፡ በመስማት ፡ ካልደከማችሁ ፡ ወደ ፡ ፕሩሲያ ፡ ታሪክ ፡ እንሂድ ። ጆዎግራፊም ፡ እንደ ፡ ጀርመን ፡ ታሪክ ፡ ማስደንገጡን ፡ አስታውሳለሁ ። ለማስተዋል ፡ ትልቅ ፡ ትምህርት ፡ ያስፈልጋል ። የሺ፡፰፻፷፮ ፡ ዓ. ም. ጦርነት ፡ ማስቸገሩን ፡ አብዝቶታል ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ሁንጋሪያ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ዋና ፡ ከተማው ፡ ማነው ፡ ? የሁንጋሪያ ፡ አየሩና ፡ መሬቱ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፪ ፤ ተራራውና ፡ ባላገሮቹስ ፡ ?

፫ ፤ የጥንቱ ፡ ባላገሮች ፡ ምንድናቸው ፡ ? መሠረታቸውስ ፡ ? ከወዴት ፡ ወገን ፡ የመጡ ፡ ይመስላሉ ፡ ?

፬ ፤ ሁንሶች ፡ ምንድናቸው ፡ ? አቲላ ፡ ማነው ፡ ? ምን ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ፡ ?

፭ ፤ ሁንጋሪያኖች ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ እንዴት ፡ ሆነው ፡ ኖሩ ፡ ? እስቴፍን ፡ ማነው ፡ ? ባ፲፰፻፵፰ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?

፮ ፤ ቦሄሚያ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ አገር ፡ ነው ? የሕዝቡስ ፡ ብዛት ፡ ? ማዕድ ንስ ፡ ? ባላገሮቹስ ፡ ?

፯ ፤ ነገደ ፡ ኬልት ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ? ባ፬፻፺ ፡ አገሩን ፡ ማን ፡ ያዘው ፡ ?

፰ ፤ ሻርለማኝ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ባ፲፰፻፮ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ? ታይሮሊስ ፡ ወዴት ፡ ኖረ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፯ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፕሩሲያ ፡ ታሪክ ።

፩ ፤ የጀርመንን ፡ ሰፊውን ፡ ክፍል ፡ ጨምሮ ፡ ከመኻከል ፡ ኤውሮጳ ፡ ሰፊ ፡ መን ግሥት ፡ የተባለው ፡ ፕሩሲያ ፡ ነው ። በያውራጃቸው ፡ የተከፋፈሉት ፡ አገሮች ፡ ቀጥለው ፡ ያሉት ፡ ፲፪ ፡ ክፍሎች ፡ ናቸው ። ዋናው ፡ ፕሩሲያ ፡ ፓስን ፤ ፓሚራ ኒያ ፤ ሲሊሲያ ፤ ብራንድቡርግ ፤ ሳክሶኒ ፤ ዊስትፋሊያ ፤ የሬኒሽ ፡ አውራጆች ። ሔሲናሶ ፤ ሀኖብር ፤ ሴልስዊግ ፤ ሆልስተን ፤ በጠቅላላው ፡ የሕዝቡ ፡ ቍጥር ፡ ከ፴፯ ፡ ሚሊዮን ፡ በላይ ፡ ነው ።

፪ ፤ ፕሩሲያ ፡ መርከብ ፡ የሚያሳልፉ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የተቀራረቡ ፡ ታላላቅ ፡ ወን ዞች ፡ አሉበት ። ስማቸውም ፡ ይህ ፡ ነው ። ናይምን ፤ ፕሬጌል ፤ ቪስቱላ ፤ አዶር ፤ ኤልብ ፤ ዌስር ፤ ራይን ፤ ሌሎችም ፡ ሞስል ፤ ላን ፡ የተባሉ ፡ ትንንሽ ፡ ወንዞች ፡ አሉበት ። ቦልቲክ ፡ አያሎች ፡ ወደ ፡ የብስ ፡ የተዘረጉ ፡ ውሃዎች ፡ አሉበት ። ዋኖቹ ፡ ተራሮች ፡ ሃርጽ ፤ ብሮከን ፤ ራይስንድበርግ ፡ ይባላሉ ። ሰፊ ፡ ደን ፡ አለባ ቸው ፤ በውስጣቸውም ፡ ፌር ፡ የሚሉት ፡ ዕንጨት ፡ (ዛፍ) ፡ ይገኛል ። ዋና ፡ ሀብቱ ፡ ከብት ፡ ማርባትና ፡ እርሻ ፡ ነው ።

፫ ፤ ሬኒሽ ፡ በሚባለው ፡ አውራጃ ፡ የሚበቅለው ፡ ወይን ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ነው ። ፕሩ ሲያ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ የሚሰጡ ፡ መቶ ፡ የሚሆኑ ፡ የሚነራል ፡ ምንጮች ፡ አሉ በት ። በበጋ ፡ ጊዜ ፡ ከኤውሮጳ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ እነዚህ ፡ ምን ጮች ፡ ወደ ፡ አሉበት ፡ ውሃ ፡ ለመጠጣት ፡ ይመጣሉ ። ሲሊሲያ ፤ ሳክሶኒ ፤ ዌስትፋ ሊያ ፤ የተባሉት ፡ አውራጃዎች ፡ ከተልባ ፡ እግር ፡ የሚሠራ ፡ ልብስ ፡ ጥሩ ፡ አድ ርገው ፡ በመሥራታቸው ፡ የተከበሩና ፡ የታወቁ ፡ ናቸው ።

፬ ፤ ቤርሊን ፡ የፕሩሲያ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ ከተማ ፡ ነው ። የተሠራ ውም ፡ እስፕሬ ፡ ከሚባል ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡ ነው ። ቤርሊን ፡ ዙሪያውን ፡ በግንብ ፡ የተከበበ ፡ ሆኖ ፡ ስድስት ፡ በር ፡ አላው ። ዳንዚክ ፡ የጥንት ፡ የፕሩሲያ ፡ የመርከብ ፡ መቋሚያ ፡ ነው ፡ በብርቱ ፡ ተመሽጓል ። አያሎች ፡ ከባዳ ፡ መድፎች ፡ ተጠምደው በታል ። ፃ ሽጉም ፡ ሰፊ ፡ ነው ።

፭ ፤ የፕሩሲያ ፡ ባላገሮች ፡ የጥንት ፡ ጀርመኖች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የጀርመንን ፡ ቋንቋ ፡ ይናገ ራሉ ። ሕዝቡ ፡ ሠራተኞች ፡ ናቸው ። ብዙ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ አቁመው ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ የተማሩ ፡ ናቸው ። ዘጠኝ ፡ ዩኒቬርሲቲ ፡ አሉዋቸው ። ስማቸውም ፡ ቤርሊን ፡ ቦን ፤ ብሬስሎ ፤ ጉቲንግን ፤ ግራይፍስዋልድ ፤ ሀል ፤ ካይል ፤ ኩኒግስ ቤርግ ፡ ይባላሉ ። የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ሁሉ ፡ የተመሠረተው ፡ በትምህርት ፡ ሚኒ ስቴርና ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጕዳይ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በያውራጃው ፡ የየራሱ ፡ ተመልካች ፡ አለው ። ከጀርመን ፡ ሕዝብ ፡ በቀር ፡ ፕሩሲያ ፤ ሌሎች ፡ አያሎች ፡ አይሁዶች ፡ አሉበት ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ፕሩሲያ ፡ እንዴት ፡ ተከፋፈለ ፡ ? የአገሮች ፡ ስም ፡ ማነው ፡ ? የሕዝብ ፡ ብዛት ፡ ?

፪ ፤ ዋናዎቹ ፡ ወንዞች ፡ እነማናቸው ፡ ? የእርሻ ፡ ሥራ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፫ ፤ ሬኒሽ ፡ የተባለው ፡ አውራጃ ፡ ስመ ፡ ጥሩነቱ ፡ በምን ፡ ነው ፡ ?
የማዕድን ፡ ምንጮች ፡ በዚያ ፡ እንዴት ፡ ናቸው ፡ ?
የተልባ ፡ እግር ፡ የሚሠራበት ፡ የታወቀው ፡ ስፍራ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?

፬ ፤ የፕሩሲያ ፡ ዋናው ፡ ከተማ ፡ ማነው ፡ ? እስፒሬ ፡ የተባለውስ ፡ ወንዝ ፡ ? ዳንትዚክ ፡ ምሽጉ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፭ ፤ የፕሩሲያ ፡ ባላገሮች ፡ እንዴት ፡ ናቸው ፡ ? ስንት ፡ የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ አሉበት ፡ ?
ስማቸውን ። ግለጽ ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ በማን ፡ ትእዛዝ ፡ ተመሥርቶ ፡ ይተዳደራል ፡ ?
አይሁድ ፡ እንዴት ፡ ናቸው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፯፩ ፡ ኤውሮጳ ።

### የፕሩሲያ ፡ ሁኔታ ።

፩ ፤ እስከ ፡ ፲፯፻—፩ ፡ ዓ. ም. ፕሩሲያ ፡ በንጉሥ ፡ የሚገዛ ፡ አገር ፡ አልነበረም ። ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በዱክ ፡ ይገዛ ፡ ነበር ። ጥንት ፡ ዘመን ፡ ባላገሮቹ ፡ ቦሩሲ ፡ ይባሉ ፡ ነበር ። አገሩ ፡ ስሙን ፡ ከዚህ ፡ አገኘና ፡ ፕሩሲያ ፡ ተባለ ።

፪ ፤ በ፲፯፻፲፫ ፡ የነገሠ ፡ ፍሬድሪክ ፡ ዊልያም ፡ ቀዳማዊ ፡ የተባለው ፡ ተሰው ፡ የማይገጥም ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ። የሚለብሰው ፡ አሮጌ ፡ ሰማያዊ ፡ ኮት ፡ ሁኖ ፡ የመዳብ ፡ አዝራር ፡ ተደርጎበት ፡ የተጌጠ ፡ ነው ። ሲለብሰው ፡ ካገጩ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ባቱ ፡ ይደርሳል ። ሌላ ፡ ባሰፋ ፡ ጊዜ ፡ ያንኑ ፡ ያረጀውን ፡ አዝራር ፡ (ቊልፍ) ፡ እንድትደረድርበት ፡ ብሎ ፡ ሰፊውን ፡ ያዘዋል ።

፫ ፤ ቁመታቸው ፡ ሰባት ፡ ፊት ፡ የሚሆኑ ፡ እጅግ ፡ ረጃጅም ፡ ሰዎች ፡ በዘበኞቹ ፡ መኻከል ፡ ይታዩ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ እርሱ ፡ በነዚህ ፡ ታጅቦ ፡ ሲሄድ ፡ በኰራት ፡ ይነፋ ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ ረጃጅም ፡ ሰዎች ፡ ከኤውሮጳ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍራ ፡ የመጡ ፡ ናቸው ። በፈቃዳቸው ፡ ባይመጡለት ፡ ሌሎችን ፡ በገንዘብ ፡ ቀጥሮ ፡ በግድ ፡ እንዲያመጡዋቸው ፡ ያደርጋል ።

፬ ፤ ፍሬድሪክ ፡ ዊልያም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ዐመል ፡ ነበረው ። በእጁ ፡ አንድ ፡ ረጅም ፡ ሽመል ፡ ይዞ ፡ በበሊርን ፡ ከተማ ፡ ጐዳና ፡ ውስጥ ፡ መሄድ ፡ ይወድ ፡ ነበር ። ሥራ ፡ የማይወድ ፡ ሰነፍ ፡ ሰው ፡ ያየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በያዘው ፡ ሽመል ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይወቃው ፡ ነበር ።

፭ ፤ ይኸው ፡ ጠባዩ ፤ ከሰው ፤ የማይገጥም ፡ ንጉሥ ፡ ሞተና ፡ ፍሬድሪክ ፡ የተባለ ፡ ልጁ ፡ ባባቱ ፡ ስፍራ ፡ ተቀመጠ ።

ይህም ፡ ከኦስትሪያ ፤ ከረሺያና ፡ ከፍራንስ ፡ ጋር ፡ ጦርነት ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስፈላጊው ፤ ገንዘብና ፡ ወታደር ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ ተረዳው ፡ ልክ ፡ የሌለው ፡ ገንዘብና ፡ ፷ ፡ ሺ ፡ ወታደር ፡ አዘጋጀ ።

፮ ፤ የፕሩሲያና ፡ የሦስቱ ፡ መንግሥታት ፡ ጦርነት ፡ ባ፲፯፻፶፮ ፡ ተጀመረ ። ይኸውም ፡ የ፯ ፡ ዓመት ፡ ጦርነት ፡ ተባለ ። ሳክሶንና ፡ ስዌድን ፡ ከፍሬድሪክ ፡ ጠላቶች ፡ ጋር ፡ ባንድነት ፡ ገጠሙ ። አንድ ፡ ጊዜስ ፡ መንግሥቱን ፡ ወደማጣት ፡ የቀረበ ፡ መስሎት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በመጨረሻው ፡ ጦርነቱን ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ክብረት ፡ ወደ ፡ አለው ፡ ፍጻሜ ፤ አደረሰው ። እርሱ ፡ በዘመኑ ፡ እጅግ ፡ የተከበረ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ። በታሪክ ፡ እንኳ ፡ ታላቁ ፡ ፍሬድሪክ ፡ ይባል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ታውቋል ።

፯ ፤ መንግሥቱን ፡ ፍሬድሪክ ፡ ሁለተኛ ፡ የተባለ ፡ የእኅቱ ፡ ልጅ ፡ ወረሰ ። ይህም ፡ ፲፩ ፡ ዓመት ፡ ገዛ ። ቀጥሎ ፡ ፍሬድሪክ ፡ ዊልያም ፡ ፫ኛ ፡ የተባለ ፡ ነገሠ ። ይህም ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ስለ ፡ ነበረው ፡ ውጊያ ፡ አማረውና ፡ ከናፖሊዮን ፡ አንደኛ ፡ ጋር ፡ መዋጋት ፡ አሰበ ።

፰ ነገር ፡ ግን ፡ ጀና ፡ ላይ ፡ በተደረገው ፡ ጦርነት ፡ ባ፲፰፻-፮ ፡ በፕሩሲያኖች ፡ ላይ ፡ አየለባቸው ። ከሞቱትም ፡ ከቈሰለኞችም ፡ ሁኖ ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ ተጐዳና ፡ አርባ ፡ ሺሕ ፡ የሚሆኑ ፡ ከተማረኩ ፡ በኋላ ፡ ፍሬድሪክ ፡ ዊልያም ፡ ከግዛቱ ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ፡ ሄደበት ።

፱ ፤ ከዋትርሉ ፡ ጦርነትና ፡ ከናፖሊዮን ፡ ከመጨረሻው ፡ ድል ፡ መሆን ፡ በኋላ ፡ ጠፍቶ ፡ የነበረ ፡ ፕሩሲያ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ማንሰራራት ፡ ጀመረ ። ፍሬድሪክ ፡ ዊልያም ፡ በጎ ፡ አሳቢ ፡ ሰው ፡ ነበር ። በምግዛው ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ በያንዳንዱ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፤ ቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ ሊኖርበት ፡ ይገባል ፡ ብሎ ፡ በግልጽ ፡ ተናገረ ። ቃሉንም ፡ እንደሚጠብቅ ፡ አምናለሁ ። ባ፲፰፻፵፩ ፡ ሞተና ፡ ፍሬድሪክ ፡ ዊልያም ፡ አራተኛ ፡ የተባለ ፡ ልጁ ፡ በስፍራው ፡ ተተካ ።

፲ ፤ ባ፲፰፻፶፰ ፡ ንጉሡ ፡ እየታመመ ፡ ጤና ፡ ስለ ፡ አልነበረው ፡ ወንድሙ ፡ የመንግሥቱ ፡ እንደራሴ ፡ ተብሎ ፡ ተሾመ ። ንጉሡ ፡ በሽታው ፡ ጠናበትና ፡ ጥር ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፷፩ ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ የመንግሥቱ ፡ እንደራሴ ፡ የነበረው ፡ ወንድሙ ፡ ዊልያም ፡ አንደኛ ፡ ወረሰው ። የበኵር ፡ ልጁ ፡ ፕሪንስ ፡ ፍሬድሪክ ፡ ዊልያም ፡ ጥር ፡ ፳፭ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፶፰ ፡ የእንግሊዝን ፡ ንጉሥ ፡ ልጅ ፡ አገባ ።

፲፩ ፤ አያል ፡ ጊዜ ፡ የሚሆን ፡ በጀርመን ፡ ልብ ፡ ክቡድ ፡ አሳብ ፡ ገባበት ። ይኸውም ፡ በአስትሪያ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥትና ፡ በፕሩሲያ ፡ ንጉሥ ፡ መኻከል ፡ ባለው ፡ ተቀዳዳሚነትና ፡ በጀርመን ፡ ነገሥታት ፡ መኻከል ፡ መሪ ፡ ስለመሆን ፡ ነገር ፡ ነበር ። ባ፲፰፻፷፮ ፡ የተደረገው ፡ ነገሩን ፡ የሚወስን ፡ አጭር ፡ ዘመቻ ፡ በፕሩሲያ ፡ ወገን ፡ ሁኖ ፡ ነገሩ ፡ አለቀ ።

፲፪ ፤ በፈረንሳይና ፣ በገዥችዋ ፣ በሕዝብዋም ፣ የመረረ ፣ ጠላትንት ፣ የተነሣው ፤ በናፖሊዮን ፣ ፩ኛ ፣ መውረርና ፣ ያን ፣ ጊዜ ፣ የነበረው ፣ የጀርመን ፣ መንግሥት ፣ በመጥፋቱ ፣ ነው ። ይኸውም ፣ ኀይል ፣ ስለ ፣ ተሰጣቸው ፣ በ፲፰፻፮ ፣ ፈረንሳዎች ፣ ጦርነት ፣ እንዲያነሡ ፣ ምንም ፣ ያገዳቸው ፣ ነገር ፣ አልነበረም ።

፲፫ ፤ ለዚሁ ፣ ነገር ፣ መላው ፣ የጀርመን ፣ ሕዝብ ፣ ተሰናዳ ። ጦራቸው ፣ በፍጥነት ፣ ተሰበሰበና ፣ ወደ ፣ ፈረንሳይ ፣ ከተጓዘ ፣ በኋላ ፣ ጠላቶቻቸውን ፣ ሁሉ ፣ አሸንፈው ፤ በዙሪያው ፣ የነበረውን ፣ ምሽግ ፣ ሁሉ ፣ አጠፉና ፣ ማረኩት ። የፈረንሳይም ፣ ንጉሥ ፣ መስከረም ፣ ፯ ፣ ቀን ፣ እጁን ፣ ሰጠ ። ፩፻፴፩ ፣ ቀን ፣ ከተከበበች ፣ በኋላ ፣ በጥር ፣ ፳፰ ፣ ቀን ፣ ፲፰፻፸፩ ፣ ከተማዪቱ ፣ ፓሪስ ፣ ተያዘች ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ፕሩሲያ ፣ መንግሥት ፣ የሆነው ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ?
አሁን ፣ እንደምን ፣ ይገዛል ፣ ? የጥንቱ ፣ ባላገሮች ፣ ማን ፣ ይባላሉ ፣ ?

፪ ፤ ፍሪድሪክ ፣ ዊልያም ፣ ቀዳማዊ ፣ የተባለው ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ሰው ፣ ነበር ፣ ?
ምን ፣ ጊዜ ፣ ነገሠ ፣ ?
ስለ ፣ ርሱ ፣ አንድ ፣ አሳብ ፣ ስጥ ።

፫ ፤ ማን ፣ ወረሰው ፣ ? ከማን ፣ ጋር ፣ ሊዋጋ ፣ አሰበ ፣ ?

፬ ፤ በ፲፯፻፶፮ ፣ ምን ፣ ጦርነት ፣ ተጀመረ ፣ ? የፍሪድሪክ ፣ ጠላቶች ፣ የትኛውን ፣ መንግሥት ፣ አጋጠሙት ፣ ?

፭ ፤ የወረሱት ፣ ሁለት ፣ ንጉሦች ፣ እነማናቸው ፣ ? ፍሪድሪክ ፣ ፪ኛ ፣ እን ደምን ፣ ሆነ ፣ ?

፮ ፤ በጀና ፣ ጦርነት ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ? ምን ፣ ሆነ ፣ ? የፕሩሲያ ፣ ንጉሥ ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ?

፯ ፤ ከዋትርሎ ፣ ጦርነት ፣ በኋላ ፣ ምን ፣ ሆነ ፣ ? ፍሪድሪክ ፣ ዊልያም ፣ ፫ኛ ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ሞተ ፣ ? ማን ፣ ወረሰው ፣ ?

፲ ፤ ጀርመንን ፣ ያልቀለለው ፣ ስለ ፣ ምንድነው ፣ ?

፲፩ ፤ ቀጥሎ ፣ ምን ፣ ሆነ ፣ ?

፲፪ ፤ ፕሩሲያኖች ፣ የጠሉት ፣ ማንን ፣ ነው ፣ ? ከዚህ ፣ የተነሣ ፣ ምን ፣ ሆነ ፣ ?

፲፫ ፤ ከፈረንሳይ ፣ ጋር ፣ የነበረው ፣ ጦርነት ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ?

## ምዕራፍ ፡ ፳፱ ፡ ኤውሮጳ ።

### የረሺያ ፡ ሁኔታ ።

፩ ፤ የረሺያ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ቱርክ ፡ አገር ፡ ግማሹ ፡ ከኤውሮጳ ፤
ግማሹ ፡ ከእስያ ፡ ነው ። በሰሜን ፡ ክፍል ፡ ያለው ፡ አገር ፡ መላው ፡ እንዳለ ፡ የረሺያ ፡
ግዛት ፡ ነው ። በዚሁ ፡ ክፍል ፡ ያሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገድ ፡ ባገሩ ፡ ላይ ፡ ተበታት
ነው ፡ ለመንጋቸው ፡ መሰማርያና ፡ ምግብ ፡ በመፈለግ ፡ ካንዱ ፡ ስፍራ ፡ ተነሥ
ተው ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ሲዛወሩ ፡ ይኖራሉ ።

፪ ፤ በሰሜን ፡ እስያ ፡ ያለው ፡ አገር ፡ በመላው ፡ ሳይቤርያ ፡ ይባላል ። አንዳች ፡
የማያበቅል ፡ ብርዳም ፡ አገር ፡ ነው ። ያን ፡ አውራጃ ፡ ባስብህ ጊዜ ፡ በብርዱ ፡
ምክያት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ትጀምራለህ ። ሕዝቡ ፡ ድኅነት ፡ ስለ ፡ ጸናባቸው ፡ የሚለ
ብሱት ፡ ያውሬ ፡ ቆዳ፤ ነው ። የሚበዙትም ፡ የሚኖሩት ፡ በትንሽ ፡ ጐጆ ፡
ውስጥ ፡ ነው ። የረሺያ ፡ ንጉሥ ፤ የሚጠላቸውን ፡ ሰዎች ፡ በግዞት ፡ እያደረገ ፡
ወደዚህ ፡ አገር ፡ ይሰዳቸዋል ።

፫ ፤ ወደ ፡ ኤውሮጳ ፡ ወገን ፡ ስላለው ፡ የረሺያ ፡ ክፍል ፡ አሁን ፡ ልንገራችሁ ፡ ነው ። እጅግ ፡
ሰፊ ፡ አገር ፡ ነው ። ስፋቱ ፡ ከአሜሪካ ፡ ዩናይትድ ፡ እስቴትስ ፡ ይተካከላል ። ተግ
ማሽ ፡ ኤውሮጳ ፡ ይሰፋል ። የሕዝቡ ፡ ቍጥር ፡ ፻፫ ፡ ሚሊዮን ፡ ይሆናሉ ።

፬ ፤ የረሺያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እጅግ ፡ ኀይለኛ ፡ መሆኑን ፡ በዚህ ፡ ታውቃላ
ችሁ ። ሕዝቡን ፡ የሚገዛ ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ነው ። ከርሱ ፡ ፈቃድ ፡ በላይ ፡ ሌላ ፡
የበለጠ ፡ ሕግ ፡ የለም ። ነገር ፡ ግን ፡ የኋለኛው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የሕዝቡን ፡
ኑሮ ፡ ለማሻሻል ፡ ፈቃድ ፡ እንዳለው ፡ አሳይቶአል ።

፭ ፤ በግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ በብዙ ፡ ስፍራ ፡ እያሉት ፡ ቤተ ፡ መንግሥቶች ፡ አሉት ፤
ነገር ፡ ግን ፡ አብዛኛውን ፡ መኖሪያው ፡ በፒትርስቡርግ ፡ ነው ። ስፍር ፡ ቍጥር ፡
የሌለው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ አለው ፤ መቸውንም ፡ ቢሆን ፡ በብዙ ፡ ወታደሮች ፡ ተከ
በና ፡ ታጅቦ ፡ ይኖራል ።

፮ ፤ በካርታ ፡ ብትመለከቱ ፡ በኤውሮጳ ፡ ያለው ፡ የረሺያ ፡ ክፍል ፡ ከሰሜን ፡ ወይም ፡
ከሰሜን ፡ ውቅያኖስ ፡ ባሕር ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ጥቍር ፡ ባሕር ፡ ያለው ፡ ስፋትና ፡
ርቀት ፡ ወደ ፡ ፪ት ፡ መቶ ፡ ማይል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታዩታላችሁ ። በምሥራቅ ፡ ወገን ፡
ከእስያ ፡ የሚለይበት ፡ ዑራል ፡ በተባለው ፡ ተራራ ፡ ነው ። በምዕራብ ወገን ፡
በፊላንድና ፡ በቦልቲክ ፡ ባሕር ፤ ከፕሩሲያና ፡ ከአውስትሪያ ፤ ከቱርክም ፡ ይዋሰናል ።

፯ ፤ ይህን ፡ ያህል ፡ ሰፊ ፡ ግዛት ፡ የሆነ ፡ አገር ፡ አየሩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሆኑን ፡ ታው
ቃላችሁ ። በበረዶው ፡ ባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ካመቱ ፡ ውስጥ ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ሙሉ ፡
ባሕሮቹ ፡ በበረዶ ፡ ይሸፈናሉ ። በመካከል ፡ ረሺያ ፡ የክረምቱ ፡ ብርታት ፡ ልክ ፡
እንደ ፡ ካናዳ ፡ ነው ። በደቡብ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ አየሩ ፡ ሙቀት ፡

ስላለው ፡ ለመኖሪያ ፡ የተስማማ ፡ ነው ። በዚህ ፡ አውራጃ ፡ ወይንና ፡ ሌላም ፡ የአ ትክልት ፡ ፍሬ ፡ በብዙ ፡ ይገኛል ።

፮ ፤ የረሺያ ፡ ዋናው ፡ ከተማ ፡ ፒትርስቡርግ ፡ የተሠራው ፡ ወደ ፡ ፊላንድ ፡ ባሕር ፡ በሚፈሰው ፡ ኔባ ፡ በሚባለው ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡ ነው ። እጅግ ፡ ኀልቶ ፡ ደምቆ ፡ የሚታይ ፡ ከተማ ፡ ነው ። ከፒትርስቡርግ ፡ የበለጠ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ የሚታይበት ፡ ስፍራ ፡ በማንኛውም ፡ ዓለም ፡ ከቶ ፡ አታገኙም ። ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ አሽከሮች ፡ ያሉዋቸው ፡ ታላላቅ ፡ ሀብታሞች ፡ ባላገሮች ፡ የሚኖሩባቸው ፡ ቤቶ ችና ፡ አያሎች ፡ የመንግሥት ፡ ቤቶች ፡ በዚህ ፡ ከተማ ፡ ይታያሉ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ የረሺያ ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? የሰሜን ፡ እስያ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ነገዶችስ ፡ ?

፪ ፡ ሳይቢሪያ ፡ የሚባል ፡ ስም ፡ የተሰጠው ፡ ለየትኛው ፡ አገር ፡ ነው ፡ ? አገሩስ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ? የሕዝብስ ፡ አኳኋን ፡ ? የረሺያ ፡ መንግሥትስ ?

፫-፬ ፤ ስለ ፡ ረሺያ ፡ ቁማር ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ ? የኤውሮጳ ፡ ረሺያ ፡ እንዴት ፡ ነው ። ? የሕዝብስ ፡ ብዛት ፡ ? በኤውሮጳ ፡ ወገን ፡ ያለው ፡ የረሺያ ፡ ስፋቱ ፡ የቱን ፡ ያህላል ፡ ? ዳርቻውስ ፡ ?

፭ ፤ በኤውሮጳ ፡ ወገን ፡ ያለው ፡ የረሺያ ፡ ግዛት ፡ አየሩ ፡ እዴት ፡ ነው ፡ ? የሚያፈራውስ ፡ ?

፮ ፤ ፒትርስቡርግ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ቤተ ፡ መንግሥቶችስ ፡ ? ሕዝቡስ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፶፫ ፡ ኤውሮጳ ።

ደግሞ ፡ ስለ ፤ ረሺያ ፡ ሁኔታ ፡ ይቀጥላል ።

፩ ፤ መስኮብ ፡ በስፋት ፡ ከፒትርስቡርግ ፡ ሁለተኛ ፡ ነው ። የረሺያ ፡ ነገሥታት ፡ የሚ ኖሩበት ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ የሆነ ፡ የቀድሞ ፡ ከተማ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ አሜሪኮች ፡ ጥንቸልና ፡ ሌላም ፡ ነገር ፡ እንዳይሸሸግበት ፡ ብለው ፡ ጥራጊውንና ፡ ጕድፉን ፡ ባንድ ነት ፡ ከምረው ፡ እንደሚያቃጥሉት ፡ እንዲሁም ፡ በ፲፰፻፲፪ ፡ ናፖሊዮንና ፡ ወታደ ሮቹ ፡ ክረምቱን ፡ እንዳይከርሙበት ፡ ብለው ፡ የከተማውን ፡ እኩሌታ ፡ አቃጥለውት ፡ ነበር ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ተሠርቶ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ቀድሞስ ፡ የመስኮብን ፡ ከተማ እንዲህ ፡ አድርገው ፡ አበላሽተውት ፡ ነበር ።

፪ ፤ ፒትርስቡርግ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ንግድ ፡ ያደርግ ፡ ነበርና ፡ የተልባ ፡ እግር ፤ ብረት ፤ ቆዳ ፤ ሞራና ፡ ሌላም ፡ ዕቃ ፡ ለማግኘት ፡ አያሎች ፡ መርከቦች ፡ ወደ ፡ ዚያ ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ መስኮብ ፡ ያለው ፡ ከባሕር ፡ ርቆ ፡ ወደ ፡ የብስ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የባሕር ፡ ንግድ ፡ ለማቆም ፡ አይመቸውም ።

፫ ፤ ይህንን ፡ ያህል ፡ ብዛት ፡ ባለው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ የነገሠ ፡ እንደ ፡ ረሺያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ያለ ፡ ከቶ ፡ በዓለም ፡ አይገኝም ። በኤውሮጳ ፡ ግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ጅንሳቸውና ፡ ነገዳቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ የሆኑ ፡ ስሳ ፡ ነገድ ፡ አሉት ። እነዚህም ፡ በቋንቋና ፡ በልማድ ፡ በኑሮዋቸውም ፡ ሁሉ ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው ። በእስያ ፡ ግዛቱ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የበለጡ ፡ ሳይኖሩት ፡ አይቀርም ።

፬ ፤ በሰሜን ፡ ኤውሮጳ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ ረሺያ ፡ ላጵላንደሮች ፡ ሳሞዶች ፡ የተባሉ ፡ ነገዶች ፡ አሉ ። እነዚህ ፡ እንደ - አራዊት ፡ ያሉና ፡ ያራዊትን ፡ ኑሮ ፡ የሚኖሩ ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ። በባሕር ፡ ጠረፍ ፡ የሚኖሩት ፡ ኑሮዋቸው ፡ ዓሣ ፡ እየተመገቡ ፡ ነው ። ሁለግዜ ፡ ዓሣ ፡ ተሸክመው ፡ የሚኖሩ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ያሣ ፡ ጠረን ፡ አላቸው ። የነዚህ ፡ ዘር ፡ ወይም ፡ ጅንስ ፡ ባሜሪካ ፡ ሰሜን ፡ የሚኖሩትን ፡ አስክዊማክስ ፡ ኤንዲያን ፡ የተባሉትን ፡ ይመስላሉ ።

፭ ፤ የጨለማው ፡ ወራት ፡ ስድስት ፤ የክረምቱ ፡ ወራት ፡ ዘጠኝ ፡ በሆነበት ፡ በብርዳም ፡ አገራቸው ፡ ለሕዝቡ ፡ ፍዝዝ ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ይሆንባቸው ፡ ይመስላል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ለነሱ ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ፡ ይታያሉ ። መጻሕፍት ፡ የሏቸውም ፡ እንጂ ፡ ተረትማ ፡ አስረዝመው ፡ ይተርታሉ ። እንደ ፡ ሌሎችም ፡ ሰዎች ፡ ያለ ፡ አሳብ ይቀልዳሉ ።

፮ ፤ በመኻከላቸው ፡ ያለፈውን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ አልጠበቁት ፡ ታሪክ ፡ የላቸውም ። አንዱ ፡ ትውልድ ፡ ሲያልፍ ፡ ሌላው ፡ ሲከተል ፡ እንዲህ ፡ እያሉ ፡ ከዘመን ፡ ወደ ፡ ዘመን ፡ ይተላለፋሉ ። ጦረኞች ፡ ስላልሆኑ ፡ በመኻከላቸው ፡ የሆነ ፡ ታላቅ ፡ የሚተረክ ፡ ነገር ፡ የለም ። ከነርሱ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ነበሩት ፡ አባቶቻቸው ፡ እነርሱም ፡ እንዲሁ ፡ ይኖራሉ ። የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ ተቀብለዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ አገሩ ፡ ብርዳም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ወደነርሱ ፡ አይሄድም ። ስለዚህ ፡ እንደ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ይኖራሉ ።

፯ ፤ በኤውሮጳ ፡ ደቡብና ፡ ምዕራብ ፡ ክፍል ፡ ባለው ፡ ረሺያ ፡ በፈጣን ፡ ፈረስ ፡ ተቀምጦ ፡ መጋለብ ፡ የሚወዱ ፡ አያሎች ፡ የታርታር ፡ ሰዎች ፡ አሉ ። ደን ፡ በተባለው ፡ ወንዝ ፡ ተከትሎ ፡ ኮሳኮች ፡ የተባሉ ፡ ዘሮች ፡ ወይም ፡ የኮሳክ ፡ ዘሮች ፡ አሉ ። እነዚህም ፡ ደግሞ ፡ ፈረስ ፡ ይወዳሉ ። በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ረጅም ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ በሚያስገርም ፡ ይዋጋሉ ። ጦር ፡ ሲወረውሩ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ፊት ፡ ርቀት ፡ ሊወረውሩ ፡ ይችላሉ ።

፰ ፤ ከነዚህም ፡ በቀር ፡ ደግሞ ፡ ብዙ ፡ አይሁዶችና ፤ አያል ፡ ሚሊዮን ፡ የሚሆኑ ፡ ፖላንዶች ፤ አያሎች ፡ ጀርመኖችና ፡ ጊብሲ ፡ የተባሉም ፡ ሁሉ ፡ በረሺያ ፡ አሉ ። በየከተሞቹ ፡ የሚኖሩ ፡ ሕዝብ ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ፡ እንደ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ይኖራሉ ። ሰውም ፡ ሁሉ ፡ የሚያፈቅረውን ፡ ሥራ ፡ እየያዘ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ይኖራል ።

፱ ፤ ከረሺያ ፡ ለም ፡ የሆነው ፡ ክፍል ፡ በፖላንድ ፡ ወሰን ፡ ወገን ፡ ያለው ፡ አገር ፡ ነው ። በዚህ ፡ ወገን ፡ ያሉት ፡ ባላገሮች ፡ በዙሪያቸው ፡ ላሉ ፡ ጐረቤቶቻቸው ፡

እህል ፡ በብዙ ፡ አድርገው ፡ ያተርፉላቸዋል ። በሰሜን ፡ ወገን ፡ ያለው ፡ አገር ፡ ብርዳም ፡ መሆኑ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ አውራጃው ፡ ረግረግ ፡ ነው ። ደን ፡ የበዛበት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የዱር ፡ አራዊት ፡ በብዙ ፡ ይገኙበታል ። ረሺያኖች ፡ ልዝብ ፡ የሆነ ፡ ጎፍላ ፡ ያውሬ ፡ ቆዳቸው ፡ እጅግ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ነው ። በብዙ ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገርና ፡ ወደ ፡ ሌላም ፡ አገር ፡ ይሰዳሉ ። የጠፍራቸውንም ፡ መልኩንና ፡ ሽታውን ፡ ልስላሴውንም ፡ በዓለም ፡ የተካከለው ፡ የለም ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ መስኮብ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ባ፲፰፻፲፪ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ?
፪ ፤ ንግድ ፡ በፒትርስቡርግ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? የመስኮብስ ፡ ?
፫ ፤ የረሺያ ፡ ክዛር ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፬ ፤ በኤውሮጳ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ ረሺያ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ነገድ ፡ ይኖራሉ ፡ ? ማንን ፡ ይመስላሉ ፡ ? ሥራቸውና ፡ ተግባራቸው ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ? ኑሮዋቸውስ ፡ ?
፭ ፤ ታርታሮች ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ? ኮዛክስ ፡ ?
፮ ፤ ሌሎቹ ፡ ባላገሮች ፡ እንዴት ፡ ናቸው ፡ ?
፯ ፤ ከረሺያ ፡ እጅግ ፡ ለም ፡ የሚባለው ፡ የትኛው ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ ? በሰሜን ፡ ወገን ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
፰ ፤ ረሺያኖች ፡ ስመ ፡ ጥሩነታቸው ፡ በምንድን ፡ ነው ፡ ? ሌሎች ፡ አገሮች ፡ የማይተካከሉዋቸው ፡ በምንድን ፡ ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፻፶፬ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፡ ታላቁ ፡ ጴጥሮስ ፡ መንግሥ ።

፩ ፤ ረሺያ ፡ ምንም ፡ ሰፊ ፡ የንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ አገር ፡ ቢሆን ፡ ታሪኩ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አይወስድብንም ። ከመቶ ፡ ዓመት ፡ የሚበልጥ ፡ እንደ ፡ አራዊት ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ ይኖሩበት ፡ ነበር ። ታላቁ ፡ ጴጥሮስ ፡ በዙፋኑ ፡ እስኪቀመጥ ፡ ድረስ ፡ በሠለጠነው ፡ ዓለም ፡ መኻከል ፡ ስፍራ ፡ ነበራቸው ፡ ተብሎ ፡ አልተነገረም ።

፪ ፤ ታላቁ ፡ ጴጥሮስ ፡ እጅግ ፡ ልዩ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ምንም ፡ መንግሥቱን ፡ ለማሠልጠን ፡ ቢጀምር ፡ በሕይወቱ ፡ ሁሉ ፡ የአውሬነት ፡ ኑሮ ፡ ይኖር ፡ ስለ ፡ ነበር ፤ የገዛ ራሱን ፡ ለማሠልጠን ፡ እጅግ ፡ የሚያስቸግር ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ ተረዳው ።

፫ ፤ የረሺያ ፡ ነገሥታት ፡ ክዛሮች ፡ ይባላሉ ። ክዛር ፡ ጴጥሮስ ፡ የ፳፭ ፡ ዓመት ፡ ጐበዝ ሳለ ፡ ዙፋኑን ፡ ተወና ፡ ዕውቀት ፡ ለማግኘት ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ኤውሮጳ ፡ ሄደ ። ሄዶም ፡ ዕውቀታቸው ፡ ከፍ ፡ ወደ ፡ አለው ፡ ዩኒቬርሲቲ ፡ (የትምህርት ፡ ቤት ፡) ገብቶ ፡ የሞቱ ፡ ቋንቋችን ፡ ለመማር ፡ አልታገለም ።

፬፤ ጴጥሮስ ፡ የፈለገው ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ትምህርት ፡ አልነበረም ። አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ ሆላንድ ፡ ሄዶና ቀየመርከብ ፡ ሥራ ፡ ለመማር ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ መርከብ ፡ ሠሪ ፡ ተጠጋ ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ይኖርበት ፡ የነበረው ፡ ቤት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ እንደ ፡ ቆመ ፤ አለ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ሄደና ፡ በሆላንድ ፡ ያደርገው ፡ የነበረውን ፡ ንግድ ፡ ተከተለ ።

፭፤ ከመርከብ ፡ ንግድ ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ የመከኒከና ፡ ትንሽ ፡ የህክምና ፡ ትምህርት ፡ ክፍል ፡ ጀመረ ። ባጭሩ ፡ ለራሱና ፡ ለአገሩ ፡ የሚጠቅም ፡ ከሆነ ፡ ማንኛውንም ፡ የዕውቀት ፡ ዐይነት ፡ አልናቀም ።

፮፤ እኅቱ ፡ የረሺያ ፡ ንግሥት ፡ ለመባል ፡ መፈተንዋን ፡ ከሰማ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በልጠ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ ይህን ፡ ወሬ ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ ትምህርቱንና ፡ ሥራውን ፡ እንዲተው ፡ ግድ ፡ ሆነበትና ፡ ወደ ፡ መስኮብ ፡ ከተማ ፡ በፍጥነት ፡ ገሠገሠ ። እንደ ፡ ደረሰም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ የዶለቱበትን ፡ ፈገደለና ፡ እኅቱን ፡ ወደ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ጨመራት ።

፯፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ትምህርቱን ለመጨረስ ፡ የሚመች ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ አላገኘ ፤ ሥራው ፡ ጦርነትና ፡ የመንግሥቱን ፡ ነገር ፡ መጠበቅ ፡ ሆነ ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እስ ቀድሞ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዕውቀት ፡ እንዳገኘ ፡ የሚያስረዳን ፡ ረሺያን ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ በማሻሻሉ ፡ ነው ።

፰፤ ጴጥሮስም ፡ መቸውንም ፡ ከማለዳው ፡ በ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ ተነሥቶ ፡ የመንግሥቱን ፡ ጕዳይ ፡ ሲሠራ ፡ ይውል ፡ ነበር ። ማታ ፡ ሥራውን ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ ጠርሙስ ፡ አረቂ ፡ በጠገቡ ፡ እስቀምጦ ፡ ዕውቀቱ ፡ እልም ፡ ብሎ ፡ እስኪ ጠፋ ፡ ድረስ ፡ ይጠጣ ፡ ነበር ።

፱፤ ሰውዬው ፡ እንኳን ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ የመጠጥ ፡ ዐመል ፡ ተጨምርበትና ፡ እንዲ ያውም ፡ ከተፈጥሮው ፡ ቍጡ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንኳን ፡ ለጠላቶቹ ፡ ቀርቶ ፡ ለወዳጆቹ ፡ የሚያስፈራ ፡ ሆነ ። መቸውንም ፡ በንግግሩ ፡ ‹ራሴን ፡ አላስተማርሁም ፡ እንጂ ፡ ረሺ ያን ፡ አስተምሬአለሁ› ፡ ይል ፡ ነበር ።

፲፤ ጴጥሮስ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ዐመል ፡ ነበረው ። ያናደዱትን ፡ ሰዎች ፡ በሽመል ፡ ይመ ታቸዋል ። የረሺያ ፡ ታላላቆች ፡ ክቡራን ፡ የሆኑ ፡ መኳንንት ፡ ይህን ፡ ቅጣት ፡ በት ዕግሥት ፡ ይቀበላሉ ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አይሁን ፡ እንጂ ፡ እቴጌዪቱ ፡ ከቴሪና ፡ የገዛ ሚስቱ ፡ እንኳ ፡ ሳትቀር ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የሚገባትን ፡ ቅጣት ፡ ታገኝ ፡ ነበር ።

፲፩፤ ከዛር ፡ ጴጥሮስ ፡ በገዛ ፡ ልጁ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ፈረደበትና ፡ በስውር ፡ እድርገው ፡ በእስር ፡ ቤት ፡ እንዲገደል ፡ አዘዘ ፡ ይባላል ። ስሙ ፡ ከነገሥታት ፡ በላይ ፡ ተጠር ቷል ፡ እንጂ ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ ተሳስቷል ። እያል ፡ ታላቅ ፡ ኃጢአት ፡ ሠርቶ ፡ በድ ሎአል ። ፡ ለዜጐቻቸው በጎ ፡ ሥራ ፡ ከሠሩት ፡ ከጥቂቶቹ ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ አንደኛው ፡ እርሱ ፡ ነው ። ከርሱ ፡ በፊት ፡ ከነበሩት ፡ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ከተነሡት ፡ ከዛሮት ፤ አብልጦ ፡ በረሺያ ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ረሺያ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ አገር ፡ ነው ፡? ታላቁ ፡ ጴጥሮስ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡?
፪ ፤ ስለ ፡ ጴጥሮስ ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡?
፫ ፤ ከዛር ፡ የተባለ ፡ ማነው ፡?
ከዛር ፡ ጴጥሮስ ፡ ዕውቀት ፡ ለመፈለግ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ተጣጣረ ፡ ተናገር ።
፰—፲ ጴጥሮስ ፡ እንዴት ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፡? ምን ፡ ልማድ ፡ ነበረው ፡ ?
፲፩ ፤ በታላቁ ፡ ጴጥሮስ ፡ ልጅ ፡ ምን ፡ መከራ ፡ ደረሰበት ፡ ?
የጴጥሮስ ፡ ጠባይ ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡?

## ምዕራፍ ፻፶፭ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፡ ታላቁ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወራሾች ።

፩ ፤ በተወለደ ፡ ባ፶፫ ፡ ዓመቱ ፡ ባ፲፯፻፳፭ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሞተና ፡ ሚስቱ ፡ እቴጌ ፡ ካቴሪን ፡ መንግሥቱን ፡ ወረሰች ። ከዛር ፡ ጴጥሮስ ፡ እርስዋን ፡ ለሚስትነት ፡ የመረጠበት ፡ ምክንያት ፡ በውበትዋና ፡ በቁንጅናዋ ፡ ተማርኮ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እርስዋስ ፡ የባላገር ፡ ልጅ ፡ ነበረች ። ባያሌ ፡ ነገር ፡ ካቴሪን ፡ እጅግ መልካም ፡ ሴት ፡ ነበረች ። ከሌላው ፡ ነገር ፡ ይልቅ ፡ ያለመጠን ፡ ወይን ፡ ትወድ ፡ ነበር ።

፪ ፤ ፪ ዓመት ፡ ብቻ ፡ ነገሠችና ፡ ጴጥሮስ ፡ ፪ኛ ፡ የተባለ ፡ የባሉዋ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ መንግሥቱን ፡ ወረሰ ። ይህም ፡ ባ፲፯፻፴ ፡ ሞተና ፡ መንግሥቱን ፡ አን (ኢዋኖና ፡) ለተባለች ፡ ለአጎቱ ፡ ልጅ ፡ ተወላት ። ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ አን ፡ መልካም ፡ ንግሥት ፡ ነበረች ። እጅግ የተ መሰገነ ፡ ሥራ ፡ ሠርታለች ። ከሠራችው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አብልጦ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ የሚያሰኛት ፡ የበረዶ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ከማሠራት ፡ የበለጠ ፡ የለም ።

፫ ፤ ይህ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ የመንግሥት ፡ ሕንፃ ፡ የተሠራው ፡ እንደ ፡ ዐለት ፡ ሁኖ ፡ በረጋው ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ ነው ። በዕንጨት ፡ ወይም ፡ በተጠረበ ፡ ደንጋይ ፡ ፈንታ ፡ በረዶው ፡ እየታነጠ ፡ ተሰበሰበ ። የቤት ፡ ዕቃና ፡ መሣሪያው ፡ ዐልጋው ፡ ሳይቀር ፡ ከበረድ ፡ ተሠራ ። ሕንፃው ፡ በስተውስጥ ፡ ሲያበራ ፤ ሲያንፀባርቅና ፡ ሲያብለጨልጭ ፡ ከሚያበራ ፡ ዕንቍ ፡ የተሠራ ፡ ይመስል ፡ ነበር ።

፬ ፤ ምንም ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ቢያበራና ፡ ቢያንፀባርቅ ፡ ከብርድ ፡ አዳራሽ ፡ ይልቅ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ የተሠራችውን ፡ ከሳሳ ፡ ጐጆ ፡ ለማደሪያዬ ፡ እመርጣለሁ ። አንባቢዎቼ ፡ ሆይ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ንግሥት ፡ አን ፡ እንደ ፡ ሠራችው ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ እንዲሁም ፡ ሌላውም ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አይመችም ። ማጌጡና ፡ ሽልማቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ብርዳም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ደስ ፡ አያሰኝም ።

፭ ፤ ከአን ፡ በኋላ ፡ ቀጥላ ፡ የታላቁ ፡ ጴጥሮስ ፡ ልጅ ፡ ኤልሳቤጥ ፡ ነገሠች ። ባ፲፯፻፵፩ ነገሠችና ፡ ፳፪ ፡ ዓመት ፡ ገዛች ። ባ፲፯፻፷፪ ፡ የነገሠ ፡ ጴጥሮስ ፡ ፫ኛ ፡ የተባለ ፡ ወራሽዋ ፡ ሆኖ ፡ ተከተላት ።

፮ ፤ እርሱም ፡ እንደ ፡ ታላቁ ፡ ጴጥሮስ ፡ ካቴሪን ፡ የተባለች ፡ ሚስት ፡ ነበረችው ። ጴጥሮስ ፡ ከመንግሥቱ ፡ እንዲሻር ፡ ካደረገች ፡ በኋላ ፡ ራስዋን ፡ የረሺያ ፡ ዋና ፡ ገዢ ፡ አደረገች ፡ እንጂ ፡ ባንድነት ፡ ሁነው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አብረው ፡ ከዙፋን ፡ አልተቀመጡም ። በኋላ ፡ ጊዜ ፡ አሳረደችውም ፡ ይባላል ።

፯ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ካቴሪን ፡ ክፉ ፡ ሴት ፡ ሳለች ፡ የሚያስገርም ፡ ስጦታ ፡ ነበራት ። በዓለም ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ የታወቀች ፡ ገዢ ፡ ሆነች ። ሁኔታዋ ፡ ሁሉ ፡ አብዛኛው ፡ እንደ ፡ ወንድ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ በወንድ ፡ ስም ፡ አድርገው ፡ ካቴሪን ፡ ታላቁ ፡ ሰው ፡ ይልዋት ፡ ነበር ።

፰ ፤ ባ፲፯፻፷፪ ፡ ካቴሪን ፡ በሞተች ፡ ጊዜ ፡ ቱርኮችን ፡ ከግዛታቸው ፡ ለማስወጣት ፡ ጥቂት ፡ ቀርቶአት ፡ ነበር ። እንዲህ ፡ በማድረጓ ፡ ገፍታ ፡ ኑራ ፡ ቢሆን ፡ በሜዴቴራኒያንና ፡ በአርክቲክ ፡ ውቂያንስ ፡ ያለውን ፡ ሰፊ ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ለመግዛት ፡ በቻለች ፡ ነበር ።

፱ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ባልዋ ፡ መታረድና ፡ ስለሌላውም ፡ በደልዋ ፡ ታላቂቱን ፡ ንግሥት ፡ ሞት ፡ አጣደፋት ። ከርስዋ ፡ በኋላ ፡ ልጅዋ ፡ ጳውሎስ ፡ መንግሥትዋን ፡ ወረሰ ። ዕድሜው ፡ ፵፪ ፡ ዓመት ፡ ነበር ።

፲ ፤ ክዛር ፡ ጳውሎስ የናቱን ፡ ስጦታ ፡ ሁሉ ፡ አላገኘም ። የተጠላና ፡ ያልተወደደ ፡ ሰው ፡ ነበር ።

ሕዝቡም ፡ አእምሮው ፡ የተበላሸ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ይጠረጥሩት ፡ ነበር ። ጠባዩ ፡ የማይስማማቸው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ መኳንንቱ ፡ ለመግደል ፡ ይዶልቱበት ፡ ነበር ።

፲፩ ፤ ጳውሎስን ፡ የበኵር ፡ ልጁ ፡ አለክሳንድር ፡ ወረሰው ። ይህም ፡ ከ፲፰፻—፩ ፡ እስከ ፡ ፲፰፻፳፭ ፡ ነገሠ ። መኻል ፡ ለመኻል ፡ በርቅሶ ፡ ወደ ፡ መስኮብ ፡ ከተማ ፡ ከነጭፍሮቹ ፡ ገብቶ ፡ ከነበረው ፡ ከናፖሊዮን ፡ ጋር ፡ ሲዋጋ ፡ ነበር ። ረሺያኖች ፡ የጥንት ፡ ከተማቸውን ፡ ስለ ፡ አቃጠሉ ፡ በከተማቸው ፡ መቃጠል ፡ የተነሣ ፡ ለፈረንሳይ ፡ ጦር ፡ ጕዳት ፡ ሆነበት ።

፲፪ ፤ ያሁኑ ፡ የረሺያ ፡ ክዛር ፡ አለክሳንድር ፡ ፪ኛ ፡ ይባላል ። ባ፲፰፻፶፭ ፡ ያባቱን ፡ የኒኮላን ፡ ዙፋን ፡ ወረሰ ። ባርነትን ፡ በማጥፋትና ፡ በመሻር ፤ የብረት ፡ መንገድን ፡ በመሥራት ፡ ዜጎቹን ፡ ደስ ፡ በማሰኘት ፡ የመንግሥቱን ፡ ሀብት ፡ ለማሳየት ፡ ተጣጣረ ። በጥር ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ባ፲፰፻፸፬ ፡ ልዕልት ፡ ማሪዬ ፡ ኤሌክሳንድሮቭና ፡ የክዛር ፡ ልጅ ፡ ለልዑል ፡ አልፍሬድ ፡ ኤርነስት ፡ አልቤርት ፡ ለኤድንቡርግ ፡ ዱክ ፡ ለግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ቢክቶሪያ ፡ ለ፪ኛው ፡ ልጅዋ ፡ ተዳረች ። በሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ መኻከል ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ እንዲሆን ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ ይህ ፡ አንድነት ፡ ፔትርስቡርግ ፡ በተባለው ፡ በታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተከበረ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ክዛር ፡ ጴጥሮስ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ? ማን ፡ ወረሰው ፡ ?
ንግሥቲቱ ፡ ካቴሪን ፡ ምን ፡ ሆነች ፡ ?

፭ ፤ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ነገሡ ቸ፡? ማን ፡ ወረሳት ፡? ጴጥሮስ ፡ ፪ኛ ፡ ምን ፡
ጊዜ፡ሞተ፡ ? ማን ፡ ወረሰው ፡ ? ንግሥት ፡ አን ፡ እንዴት፡ሆነች ፡ ?
ከበረዶ ፡ ስለ ፡ ተሠራው ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተናገር ።

፮ ፤ ንግሥት ፡ አን ፡ መንግሥቷን ፡ ማን፡ወረሳት ፡ ?
ጴጥሮስ ፡ ፫ኛ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነገሠ ፡ ?

፯ ፤ የርሱ፡ሚስት ፡ እንዴት ፡ ሆነች ፡ ? ስለርሷ ፡ ምን፡ትላለህ ፡ ?

፰ ፤ ካቴሪን ፡ ታላቂቱ ፡ ሳትሞት ፡ ያሰበችው፥ ምን ፡ አሳብ ፡ ኑርዋታል ፡ ?
ምን ፡ ጊዜ ፡ ሞተች ፡ ?

፱ ፤ መንግሥቷን ፡ ማን፡ወረሳት ፡ ?

፲ ፤ ከዛር ፡ ጳውሎስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፲፩ ፤ ማን ፡ ወረሰው ፡ ? አለክሳንድር ፡ እንዴት፡ሆነ ፡ ?
የፈረንሳይ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ እንደምን፡ፈረሰ ፡ ?

፲፪ ፤ የዛሬው ፡ የረሺያ ፡ ከዛር፡ማነው ፡ ?
እንደምን፡ሆነ፧ ?
ልጁን፡ማን ፡ አገባት ፡ ?